በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርስቲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን ፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል::

የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ዩኒቨርስቲው ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው:: ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የዩኒቨርስቲው የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

1. ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/3 (ሸ) መሠረት አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን፣ የምክር አገልግሎቱን፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራውን ወይም አገልግሎቱን አጠናቅቆ ባያስረክብ፣ ላዘገየበት ጊዜ የሚወሰደው እርምጃ በአቅራቢውና በመንግሥት መ/ቤት መካከል በሚደረግ ውል መካተት እንዳለበት የተገለጸ ሲሆን በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/4/ሀ መሰረት ደግሞ ከፍ ሲል በመመሪያው አንቀጽ 16.27.3 (ሸ) መሠረት አቅራቢዎች ግዴታቸውን ባይወጡ ግዴታቸውን ሳይወጡ ለዘገዩበት ጊዜ ሳይፈጽሙ በቀረው የውል መጠን ላይ በየቀኑ 1/1000ኛ መቀጣት እንዳለባቸው የተደነገገ ቢሆንም፣ በድምሩ ብር 617,590.58 የተለያዩ ዕቃዎችን በውሉ መሠረት ገቢ ሳያደርጉ ከውል በላይ ካዘገዩ አቅራቢዎች ላይ ገቢ መሆን የነበረበት የጉዳት ካሳ ለመንግሥት ገቢ አለመደረጉ፣

2. በፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 8 (ሀ) መሠረት የመንግሥት ገንዘብ ለፀደቀው ዓላማና በተፈቀደው መጠን ብቻ ጥቅም ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ለዩኒቨርሲቲ መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ የድልድል ስራ ለሰሩ ኮሚቴዎች ለማበረታቻ በሚል የተጣራ ብር 71,500.00 እና ለግዥ አጽዳቂ፣ ለስተዳደር ዲሲፒሊን፣ ለቅሬታ ሰሚ፣ ለቋሚ፣ ለአላቂ እና ለተማሪዎች ምግብ ቤት ዕቃ ቆጣሪ፣ እንዲሁም ለቴክኖሎጂ (IOT) ኮሚቴዎች የተጣራ ብር 148,429.45፣ በድምሩ ብር 219,929.45 በመንግሥት የወጣ መመሪያና የክፍያ ተመን ሳይኖረው ለማበረታቻ በሚል መከፈሉ፣

3. ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ህዳር 18 ቀን 2005 ዓ.ም በቁጥር መ80-839/1 በተፃፈ ደብዳቤ ዘላቂነት ባለውና በተመደበ የሥራ መደብ ላይ በኮንትራት (በጊዜያዊነት) በፌዴራል የመንግሥት መ/ቤቶች ተቀጥረው ያልተቋረጠ አገልግሎት ሲሰጡ የቆዩ ሠራተኞች በቋሚነት እንዲመደቡ፣ በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ባልተመደበና ዘላቂነት በሌለው የሥራ መደብ ላይ በኮንትራት /በጊዜያዊነት/ ተቀጥረው የነበሩ ሠራተኞች ቅጥር እንዲቋረጥ ሆኖ በአስቸኳይ መሰናበት እንዳለባቸው፣ ይህ መመሪያ ለአንድ ጊዜ አፈፃፀም ብቻ የሚያገለግል ሲሆን ከየካቲት 30/2005 ዓ.ም በኋላ ተግባራዊ ማድረግ እንደማይቻል እንዲሁም እጅግ አስፈላጊ ለሆነና ለአጭር ጊዜ ብቻ የኮንትራት/ጊዜያዊ ቅጥር መፈጸም አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ ጥያቄው በመጀመሪያ ለሲቪል ሠርቪስ ሚኒስቴር ቀርቦ ተቀባይነት ማግኘት እንዳለበት መመሪያ የተላለፈ ቢሆንም፣ በዩኒቨርሲቲው የሚገኙ የኮንትራት/ጊዜያዊ ሠራተኞች በቋሚ የሥራ መደብ ላይ በቋሚነት ሳይመደቡ ወይም ዘላቂነት ከሌለው የሥራ መደብ ላይ ሳይሰናበቱ እና ዩኒቨርሲቲው በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል ጠይቆ ሳያስፈቅድ ለኤሌክትሪክ፣ ለቧንቧ፣ ለግቢ ጸጥታ፣ ለካፍቴሪያ፣ ለዉሃ ኦፕሬተር እና ለወጥ ቤት ሠራተኞች በበጀት ዓመቱ በሂሳብ መደብ 6114 (የቀን ሠራተኞች ምንዳ) በድምሩ ብር 1,803,491.00 የተከፈለ መሆኑ፣

4. ዩኒቨርሲቲው ለተማሪዎች ምግብ ማብሰያ አገልግሎት የሚውል የማገዶ እንጨት ለመግዛት ባወጣው ጨረታ አንድ ሜትር ክዩብ የማገዶ እንጨት በብር 580.00 ለማቅረብ ጨረታውን ተወዳድሮ ያሸነፈው አንድ አቅራቢ በ11/02/09 ውል የፈረመ እንዲሁም በዕለቱ 30% ቅድሚያ ክፍያ እንዲሰጠው የጠየቀ ቢሆንም ግልጽ ባልሆነ ምክንያት ቀደም ሲል የማገዶ

እንጨቱን ሲያቀርብ የነበረ ድርጅት እንዲያቀርብ በመደረጉ፣ በድምሩ የብር 330,976.58 ግዥ ያለአግባብ በብልጫ የተፈጸመ መሆኑ፣

5. ክፍያዎች ከመፈጸማቸው በፊት በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 9 ላይ የተጠቀሱ ጥንቃቄዎች መደረጋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ለዩኒቨርሲው ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩቱ ማስፋፊያ ለግንባታ ለሚሆን መሬት ለተፈናቃዮች ካሳ ክፍያ ብር 34,519,384.53 ወጪ ተደርጎ ወደ ድሬዳዋ ከንቲባ ጽህፈት ቤት የባንክ ሂሳብ ገቢ የተደረገ ሲሆን፣ ግምቱ የተደረገበትና ለክፍያ የቀረበው ሰነድ የብር 34,469,487.49 በመሆኑ በብልጫ ብር 49,897.04 (34,519,384.53 - 34,469,487.49) ወደ ከንቲባ ጽህፈት ቤቱ የባንክ ሂሳብ ገቢ የተደረገ መሆኑ፣
6. ስለፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 ክፍል ሦስት አንቀጽ 12 የመንግሥት ገንዘብ ክፍያ ሊፈጸም ወይም ወጪ ሊደረግ የሚችለው የተፈቀደ በጀት ሲኖር ብቻ እንደሆነ የሚገልጽ ቢሆንም በብር 1,868,905.24 የተገዙ የኤሌክትሪክ እና የኤሌክትሮኒክ ዕቃዎች ገቢ የተደረጉት በቀን 21/10/08 (2008 በጀት ዓመት) ቢሆንም ክፍያው በ2009 በጀት ዓመት ተፈጽሞ ወጪው በቀን 19/12/08 ዓ.ም (2009 በጀት ዓመት) በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 456752 የተመዘገበ በመሆኑ በ2008 በጀት ዓመት የተገዛውና ገቢ የተደረገው ዕቃ በ2009 በጀት ዓመት በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፣
7. የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 6 የመንግስት መ/ቤቶች በጀት ክፍያ የሚፈጸመው ወይም ወጪ የሚደረገው የተፈቀደ በጀት ሲኖር ብቻ መሆኑን የሚገልጽ እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 39/2006 አንቀጽ 5/4 በመንግሰት ውሳኔ የተሰጠባቸው እንደ የተማሪዎችና የህሙማን የምግብ በጀት ተመን የመሳሰሉት ወጪዎች ከውስጥ ገቢ ከተመን በላይ መጠቀም እንደማይቻል የተገለጸ ቢሆንም፣ ለተማሪዎች ምግብ የሚውል የምግብ ዘይት ከሀማሬሳ የምግብ ዘይት አክሲዮን ማህበር በድምሩ ብር 231,731.40 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 39/2006 ከሚያዘው ውጭ እና አስቀድሞ በተፈቀደ በጀት ሳይያዝ ከውስጥ ገቢ ሂሳብ መከፈሉ፣
8. እስከበጀት ዓመቱ መጨረሻ መወራረድ ሲገባ ያልተወራረደ ብር 46,589,112.78 ተሰብሳቢ እና ብር 561,546.41 ተከፋይ ሂሳብ መኖሩ፣ በተጨማሪም ከውዝፉ ተሰብሳቢ

ሂሳብ ውስጥ በሂሳብ መደብ 4251 ከተያው ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 30,057,204.80 ውስጥ በGIZ-IS ስም የተያዘው ብር 25,112,475.60 ዝርዝር ሁኔታ ሲጣራ፣

- ዩንቨርሲቲው በGIZ-IS አስተባባሪነት በግቢው ውስጥ ለሚያስገነባው የፍሳሽ ውኃ ማጣሪያ ፕላንት ሥራ በቅድሚያ ክፍያ መልክ የከፈለዉና ወደ 2009 በጀት በዓመት የዞረዉ ጠቅላላ የብር 43,224,976.87 ሲሆን በ2009 በጀት ዓመት ብር 5,580,000.00 ተጨምሮለት በጠቅላላዉ ብር 48,804,976.87 የቅድሚያ ክፍያ በ4251 ሂሳብ ተይዞ የተሰጠው ሲሆን እስከ ሰኔ 30/2009 ፕሮጀክቶቹ በመጠናቀቃቸው የመያዣ ሂሳቡ /retention/ ለሥራ ተቋራጩ የተመለሰለት ቢሆንም ከጠቅላለው በ4251 በድርጅቱ ስም ተይዞ የነበረው የቅድሚያ ክፍያ ብር 48,804,976.87 ውስጥ ብር 23,692,501.26 ብቻ ተወራርዶ በወጪ የተያዘ ሲሆን ብር 25,112,475.61 ሳይወራረድ /ከድርጅቱ ሳይሰበሰብ/ የፕሮጀክቱ ሥራ የተጠናቀቀ መሆኑ፣

9. ከመደበኛ በጀት ብር 8,610,801.77 እና ከውስጥ ገቢ ሂሳብ ብር 1,059,558.59፣ በድምሩ ብር 9,670,360.36 ከተፈቀደው በጀት በላይ ሥራ ላይ የዋለ መሆኑ፣ በተጨማሪም ከውስጥ ገቢ ሂሳብ ከበጀት በላይ ከወጣው ብር 1,059,558.59 ውስጥ በሂሳብ መደብ 6211 የወጣው ብር 8,648.00 እና በሂሳብ መደብ 6216 የወጣው ብር 231,731.40፣ በድምሩ ብር 240,379.40 አስቀድሞ በጀት ሲደለደል በጀት ባልተያዘባቸው የሂሳብ መደቦች ላይ የወጣ መሆኑ፣

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 9 በዝርዝር በተገለጹት ምክንያቶች በእኛ አስተያየት የዩኒቨርስቲው የሂሣብ መግለጫዎች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበውን ገቢ፣ የተፈፀመውን ወጪና የበጀት አጠቃቀሙን በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም፣ ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገባቸው ጉዳዮች (Emphasis of Matters)

1. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ምዕራፍ 6 አንቀጽ 52/1(ሀ) ላይ የመንግስት መ/ቤቶች ከአንድ አቅራቢ ግዥ መፈጸም የሚችሉት ዕቃው፤ የግንባታ ዘርፍ ሥራው፤ የምክር ወይም ተፈላጊው ሌላ አገልግሎት

የሚገኘው ከአንድ ዕጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ እንደሆነ የተገለጸ ቢሆንም፣ በድምሩ የብር 1,898,354.78 ግዥ ያለምንም ውድድር በቀጥታ ግዥ የተፈፀመ መሆኑ፣

2. ሰኔ 2002 በወጣው የግዥ መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 15.3 እና 15.4 በአዋጁ እና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግሥት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልጽ ጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው እና ከግልጽ ጨረታ ውጭ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈጸም የሚችሉት በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተገለጹት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ እንደሆነ እንዲሁም ከታህሳስ 12/2008 ጀምሮ ሥራ እንዲውል በተሻሻለው የፌዴራል መንግስት የግዥ መመሪያ አንቀፅ 24.2 መሰረት በፕሮፍርማ የሚገዛ ዕቃ ግዥ ጣሪያ እስከ ብር 200,000.00 እንደሆነ፣ በዚሁ መመሪያ አንቀጽ ቁጥር 24.12 ላይ ደግሞ የመንግስት መ/ቤቶች በአንድነት ሊፈፀሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ከፋፍለው መግዛት እንደሌለባቸው የተገለጸ ቢሆንም፣
   - ለመዝናኛ ክበብ አገልግሎት የሚውሉ የብር 397,600.01 ጠረጴዛዎች፣ ወንበሮችና ሶፋዎችን በጨረታ የግዥ ዘዴ መግዛት ሲገባ ግዥዉን በብር 143,640.01፣ ብር 58,320.00 እና ብር 195,640.00 በመከፋፈል በተመሳሳይ ቀን (በ18/02/09) ሶስት የዋጋ ማቅረቢያ በመሰብሰብ በቀን 23/03/09 ከዋሪት ሙሉ ጥላ ኢንተርናሽናል ኃ.የተ.የግል ኩባንያ በሁለት ጊዜ በብር 143,640.1 እና በብር 58,320.00፣ በድምሩ በብር 201,960.01፣ ከSUNJUN BO FURNITURES PRODUCTION ደግሞ በብር 195,640.00፣ ግዡው 3 ቦታ ተከፋፍሎ በዋጋ ማወዳደሪያ መፈጸሙ፣

3. FE Construction የተባለ ተቋራጭ ቀድሞ የወሰዳቸውን ግንባታዎች በተሰጠዉ የጊዜ ገደብ ውስጥ አጠናቅቆ ሳያስረክብ ሌሎች የተለያዩ የግንባታ ሥራዎች በተደራራቢ የተሰጡት በመሆኑ ሥራዎቹ እየተጓተቱ ሲሆን በዚህም ምክንያት የካቲት/2007 እና መጋቢት/08 መጠናቀቅ የነበረባቸው ግንባታዎች እስከ የካቲት 30/2009 ዓ.ም ድረስ ያልተጠናቀቁና የውል ማራዘሚያ ጊዜ እየተጠየቀባቸው መሆኑ፣

4. ከመደበኛ በጀት ብር 19,982,427.02፣ ከካፒታል በጀት ብር 124,431,172.13 እና ከውስጥ ገቢ ብር 51,843.61፣ በድምሩ ብር 144,465,442.76 በየሂሳብ መደቡ ከ10% በላይ ያልተሰራበተት በጀት መሆኑ፤

ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)

ቋሚ ንብረት

- በቋሚ ዕቃ ግምጃ ቤት የንብረት ገቢ ሞዴል 19 እና ወጪ ሞዴል 22 የሚሰራው በአንድ ሰራተኛ ብቻ መሆኑ፤
- የእስቶክ ካርድና የቢን ካርድን ጨምሮ ምንም ዓይነት ንብረት ምዝገባ የማይከናወን በመሆኑ ያለውን ባላንስ /ሚዛን/ ለማወቅ የማይቻል መሆኑ፤
- የበጀት ዓመቱ ዓመታዊ ንብረት ቆጠራ ያልተካሄደ መሆኑ፤
- አዲስ አገልግሎት ላይ ያልዋሉ በቁጥር ወደ 20 የሚሆኑ UPS ያለ አገልግሎት በእስቶር ውስጥ ያሉ መሆኑ፤
- በቁጥር 200 የሚሆኑ ያገለገሉ ግን የአገልግሎት ጊዜያቸው ያላበቃ የካፍቴሪያ ወንበሮች ያለስራ አስቶር ወስጥ መሆናቸው፤
- ብረት ድስት፤ የሻይ ማንቆርቆሪያ፤ የመመገቢያ ሰሀን የመሳሰሉት በርካታ ቁጥር ያላቸው የምግብ ቤት ዕቃዎች አገልግሎት ያቆሙ ቢሆንም ሳይወገዱ ሜዳ ላይ የተቀመጡ መሆኑ፤
- እንደ ቁም ሳጥኖች፤ ጠረጴዛዎች፤ ወንበሮችና ሌሎች የተለያዩ ቁሳቁሶች መወገድ እያለባቸው ሳይወገዱ ተበታትነው ሜዳ ላይ የሚገኙ መሆኑ፤

አላቂ ንብረትን በተመለከተ

- ብዛታቸው 700 የሚሆን ለሰራተኞች የደንብ ልብስ ተብሎ የተገዙ የወንድና የሴት ጥንድ ጨማዎች ለሰራተኛው ሳይከፋፈል ከ2 ዓመት በላይ ያለአገልግሎት እስቶር ወስጥ የተከማቹ መሆኑ፣

የተማሪዎች ክሊኒክ መድኃኒት ክፍልን በተመለከተ

- የመድኃኒት አጠቃቀምን በተመለከተ የገቢና የወጪ አጠቃቀም በወሩ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት የማይደረግ መሆኑ፤

ተሽከርካሪ መኪና

- አንድ Mistubish pick up ተጋጭቶ ከአንድ ዓመት በፊት በኢትዮ ኒፖን (Ethionipon) ለጥገና እንደገባና እስከአሁን ተጠግኖ ያልወጣ መሆኑ፤

<u>እርምጃ ያልተወሰደበት የ2008 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝትና የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ከዩኒቨርስቲ የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ውስጥ፤

- ለፍሳሽ ውሃ ማጣሪያ ፕላንት ግንባታ ስራ በ30/10/08 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 554654 ለአዲስ ገላው ለሕንጻ ስራ ተቋራጭ በምስክር ወረቀት /payment certificate/ 33 እና 34 የተከፈለ ብር 17,943,350.74 ውስጥ ለብር 16,732,085.40 እና ለግንባታ ሥራ ከውጪ ተገዝተው የገቡ የግንባታ ዕቃዎች ማጓጓዣ ለአንለይ አለሙ የደረቅ ጭነት ማመላለሻ ድርጅት ከተከፈለው ብር 2,201,216.24 የብር 1,705,431.54 የክፍያ ደረሰኝ ያልቀረበላቸው መሆኑ፣
- የዕቃ ግዥና የህንጻ ግንባታ የጉዳት ካሳን በተመለከተ መላክ የት/ቤት ላብራቶሪ ዕቃዎች ጅምላ አከፋፋይ ኃ/የተ/የግል ማህበር ከተቋሙ ጋር በገቡት ውለታ መሰረት ባለመፈጸማቸው ከአቅራቢዎቹ ያልተሰበሰበ የጉዳት ካሳ ብር **69,331.00** ያልተሰበሰበ መሆኑ፣
- ዩኒቨርሲቲው በውሉ መሰረት በተቀመጠው የማስረከቢያ ቀን መሰረት ግንባታውን አጠናቀው ያላስረከቡ 5 የህንጻ ተቀራጮች የህንጻ ግንባታውን ላዘገዩበት የጉዳት ካሳ/ቅጣት/ በድምሩ ብር 22,945,687.00 እንዲከፍሉ ያላደረገ መሆኑ፣

በሚሉ ግኝቶች ላይ እስከ 2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ማብቂያ ጊዜ 25/03/2010 ድረስ እርምጃ ያልተወሰደባቸው መሆኑ፣

የፌደራል ዋና ኦዲተር መ /ቤት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች

መግቢያ፤

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የድሬ ዳዋ ዩኒቨርሲቲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዩኒቨርስቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓላማ፤

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የዩኒቨርስቲው የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት፤

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሰረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመስራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፣

- የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ ሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ፣ያጠቃልላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡ አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡ ይሁን እንጂ ኦዲቱ በድሬ ዳዋ ዩኒቨርሲቲ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡ የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የተቋሙ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. <u>የገቢ ሂሳብ፣</u>

1.1 <u>ያልተሰበሰበ የጉዳት ካሳ፣</u>

1.1.1 <u>ግኝት፣</u>

ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/3 (ሸ) መሠረት አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን፣ የምክር አገልግሎቱን፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራውን ወይም አገልግሎቱን አጠናቅቆ ባያስረክብ፣ ላዘገየበት ጊዜ የሚወሰደው እርምጃ በአቅራቢውና በመንግሥት መ/ቤት መካከል በሚደረግ ውል መካተት እንዳለበት የተገለጸ ሲሆን በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/4/ሀ መሰረት ደግሞ ከፍ ሲል በመመሪያው አንቀጽ 16.27.3 (ሸ) መሠረት አቅራቢዎች ግዴታቸውን ባይወጡ ግዴታቸውን ሳይወጡ ለዘገዩበት ጊዜ ሳይፈጽሙ በቀረው የውል መጠን ላይ በየቀኑ 1/1000ኛ መቀጣት እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡

በዚህ መሰረት ኦዲት ሲደረግ፡-

በዋናው ግቢ፣

- ከማሽ የጽህፈትና የኮምፒዩቴር ዕቃዎች መሸጫ ድርጅት ብር 16,247.54፣
- ከሪልየብል የትምህርት መሳሪያዎች አቅራቢ ብር 32,835.66፣
- ከታፍ ኮሚሽን መጽሃፍ አቅራቢ ብር 31,442.24፣
- ከመስፍን ዘለቀ ጨርቃ ጨርቅ እና የደንብ ልብስ ስፌት ብር 31,198.40፣
- ከኢፋት ጨርቃ ጨርቅ ብር 14,603.70፣
- ከሱሜያ ስሃምና ጓደኞቹ የልብስ ስፌት ማህበር ብር 8,614.30፣
- ከቃሊቲ ኮንስትራክሽን ዕቃዎች ማምረቻ ብር 141,413.78፣
- ከሮያል ፎም እስፓሪንግ ፍራሽና ፕላስቲክ ውጤቶች ማምረቻ ብር 23,339.94፣

በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፣

- ከA.L.G Trading የተለያዩ የICT ዕቃዎችን አቅራቢ ብር 48,328.12፣
- ከሲምቦል ቴክኖሎጂስ የተለያዩ የICT ዕቃዎች አቅራቢ ብር 284,170.60፣

በድምሩ ብር 617,590.58 የተለያዩ ዕቃዎችን በውሉ መሠረት ገቢ ሳያደርጉ ከውል በላይ ካዘገዩ አቅራቢዎች ላይ ገቢ መሆን የነበረበት የጉዳት ካሳ ለመንግሥት ገቢ አለመደረጉ ተረጋግጧል፡፡

1.1.2 ስጋት፣

- አስፈላጊነታቸው በመንግስት ታምኖበት የወጡ አዋጆች ደንቦችና መመሪያዎችን መተላለፍ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡
- አቅራቢዎቹ መክፈል የሚገባቸውን የጉዳት ካሳ እንዲከፍሉ ባለመደረጉ መንግስት ያገኝ የነበረዉን ገቢ ሊያጣ ይችላል፡፡

1.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- ያልተሰበሰበው ቅጣት ከሚመለከታቸው ላይ ገቢ እንዲሆን ተደርጎ ለወደፊቱ ዩኒቨርሲቲው ኃላፊነታቸውን የማይወጡ አቅራቢዎችን በመመሪያው መሠረት ሊቀጣቸው የሚገባ ሲሆን በተደጋጋሚ ኃላፊነታቸውን የማይወጡትን ደግሞ ለመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በማሳወቅ ተጨማሪ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

1.1.4 የሥራ አመራሩ ምለሽ፣

የሥራ አመራሩ ከቃሊቲ ኮንስትራክሽን ዕቃዎች ማምረቻ መሰብሰብ ስላለበት የጉዳት ካሳ ምላሽ ያልሰጡ ሲሆን፣

- የጉዳት ካሳን በተመለከተ አቅራቢዎች በውላቸው መሰረት በወቅቱ ውል ግደታቸዉን ባለመወጣታቸው ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ጉዳት ካሳ ተቀናሽ ባለመደረጉ መንግስት ሊገኝ የሚገባውን ጥቅም ያጣ በመሆኑ ይህን ጥቅም ያገኝ ዘንድ በተገቢው መንገድ ጥያቄው እንዲቀርብ የሱመያ፡ የኢፋት ጨርቃ ጨርቅ፡ የመስፍን ዘለቀ፡ የታፍ ኮሚሽን ኤጀንት፡ የሪሊያብል፡ የማሽ የፅህፈት፡ የሮያል ፎም ለዩኒቨርሲቲው የሕግ እና አስተዳደር ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት አሳልፈው የሰጡ መሆናቸውን፣
- ALG ትሬዲንግ 80% ንብረቶች በጊዜው ገደብ በ9/12/08 ገቢ ያደረገ እና ለስራ ማስኬጃ ቅድመ ክፍያ ያልጠየቀ ሲሆን የቀሩትን ሶስት ዕቃዎች ለማስገባት የ45 ቀናት ማራዘሚያ በውጭ ምንዛሬ እጥረት ምክንያት እንዲራዘምለት በጠየቀው እና ለማኔጅመንት ቀርቦ በተወሰነለት መሰረት የተጠበቀ እና በጎን

ፕሮጀክታቸውን እየሰሩ በመጠባበቅ ላይ የነበሩ ሆኖ በተባለው ቀን ባያደርስላቸውም ጨረታ ድጋሚ ማውጣት የበለጠ ስለሚጎዳ በትዕግስት በመከታተል ለፕሮጀክቱ ማጠናቀቅ ስለሚፈልጓቸው በዚሁ ቀን (acceceries) ያስገባላቸው ሲሆን ለቀሪ እቃዎች ከጥቅምት በኋላ ለገቡት ቅጣት መቀጣት የነበረበት መሆኑን ለመገንዘብ መቻላቸውን፣ በመሆኑም የተጠቀሰው የጉዳት መጠን ባይሆንም መቀጣት እንደነበረበት ትምህርት የወሰዱ መሆኑን፣

- ሲምቦል ቴክኖሎጂስ በውሉ መሰረት ዕቃው መግባት የነበረበት በ02/01/09 ቢሆንም ድርጅቱ ለ90 ቀን የይራዘምልኝ ጥያቄ በውጭ ምንዛሬ እጥረት ምክንያት ያቀረበ በመሆኑ ማናጅመንቱ ለ60 ቀናት የፈቀደለት ሲሆን አሁንም ድርጅቱ በሌላ ደብዳቤ የ30 ቀናት ማራዘሚያ መጠየቁና ዕቃዎቹ በከፊል የገቡ በመሆኑ በመታገስ እቃዎች በተፈቀደለት አጠቃላይ የ90 ቀናት ማራዘሚያ በ02/04/09 ማስገበት ሲኖርበት በ08/04/09 ያስገባ በመሆኑ ለ6 ቀናት የጉዳት ካሳ ብቻ ያልተቀጣ እንጂ እንደተገለፀው ለ106 ቀናት አለመሆኑን፣ ለዚህም በማኔጀመንቱ እያቀረቡ እያስወሰኑ እና ተገቢውን ክትትል እያደረጉበት የነበረ ግዥ መሆኑን፣

ለሥራ አመራር ደብዳቤ በላኩት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

2. <u>የወጪ ሂሳብ</u>፣

ለተለያዩ አገልግሎቶች የዋለው የወጪ ሂሳብ በፌዴራል መንግስት ታምኖበት በወጡ አዋጆች፤ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱ ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

2.1 <u>በመንግሥት የወጣ ተመን ሳይኖረው ለልዩ ልዩ ማበረታቻዎች የተከፈለ ሂሳብ</u>፣

2.1.1 <u>ግኝት</u>፣

በፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 8 (ሀ) መሠረት የመንግሥት ገንዘብ ለፀደቀው ዓላማና በተፈቀደው መጠን ብቻ ጥቅም ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- የዩኒቨርሲቲው ማነጅመንት በቀን 03/09/2009 ባደረገው 13ኛ መደበኛ ስብሰባ ከ1ኛ ዙር እስከ 3ኛ ዙር ድረስ የሠራተኞች ድልድል ላከናወኑ ኮሚቴዎች ማበረታቻ እንዲከፈል መወሰኑ ተጠቅሶ ለአስተዳደርና ልማት ም/ፕረዝዳንት በ14/10/2009 በቁጥር ድ/ዳ/ዩ/102/192/2009 በተጻፈው ደብዳቤ መሠረት በ19/10/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ

ቁጥር 458893 በሂሳብ መደብ 6417 ለዩኒቨርሲቲ መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ አንደኛና ሁለተኛ የድልድል ስራ ለሰሩ ኮሚቴዎች ለማበረታቻ በሚል

ተ.ቁ	ገንዘቡን የተቀበሉ ሰዎች ብዛት	የገንዘቡ ልክ	ተቀናናሽ	የተጣራ ተከፋይ
1	1	10,000.00	0	10,000.00
2	2	8,000.00	0	16,000.00
3	5	7,000.00	0	35,000.00
4	3	3,500.00	0	10,500.00
			ድምር	71,500.00

የተጣራ ብር 71,500.00፣

- በቀን 26/07/09 በሳጥን ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0702132 በሂሳብ መደብ 6417 ለግዥ አጽዳቂ፣ ለስተዳደር ዲሲፒሊን፣ ለቅሬታ ሰሚ፣ ለቋሚ፣ ለአላቂ እና ለተማሪዎች ምግብ ቤት ዕቃ ቆጣሪ፣ እንዲሁም ለቴክኖሎጂ (IOT) ኮሚቴዎች

ተ.ቁ	ገንዘቡን የተቀበለ ሰዎች ብዛት	የአንድ ሰው ያልተጣራ ክፍያ	ጠቅላላ ያልተጣራ ክፍያ	የሥራ ግብር	የተጣራ ክፍያ
1	13	10,470.00	136,110.00	47,359.00	88,751.00
2	6	6,036.00	36,216.00	10,687.20	25,528.80
3	4	2,872.00	11,488.00	2,330.80	9,157.20
4	1	8,310.00	8,310.00	2,779.00	5,531.00
5	1	7,647.00	7,647.00	2,506.15	5,140.85
6	1	1,370.00	1,370.00	191.5	1,178.50
7	2	2,197.00	4,394.00	778.5	3,615.50
8	1	2,514.00	2,514.00	468.5	2,045.50
9	1	3,278.00	3,278.00	720.9	2,557.10
10	1	1,586.00	1,586.00	234.7	1,351.30
11	1	4,867.00	4,867.00	1,294.30	3,572.70
		51,147.00	217,780.00	69,350.55	148,429.45

የተጣራ ብር 148,429.45 (ያልተጣራ ብር 217,780.00) ፣ በድምሩ ብር 219,929.45 በመንግሥት የወጣ መመሪያና የክፍያ ተመን ሳይኖረው ለማበረታቻ በሚል ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

2.1.2 ስጋት፤

ማናቸውም ክፍያ በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት ካልተፈጸመ የመንግስት ሀብት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፣ ተጠያቂነትንም ያስከትላል፡፡

2.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፤

- ገንዘቡ ያለአግባብ የተከፈለ ስለሆነ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ላይ ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ለወደፊቱ ተመሳሳይ ጉዳይ ሲያጋጥም ክፍያዎቹን መመሪያ በሚፈቅደው መሠረት መፈጸም ወይም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት በልዩ ሁኔታ ማስፈቀድ ያስፈልጋል፡፡

2.1.4 የሥራ አመራሩ ምለሽ፤

የሥራ አመራሩ፣

- የማበረታቻ ክፍያውን በተመለከት ዩኒቨርሲቲው በተለያዩ የስራ ሂደቶች ውስጥ ከመደበኛ የስራ ሰዓታቸው ውጪ ቅዳሜና እሁድን ጨምሮ መምህራንና ሰራተኞች በተለያዩ ኮሚቴዎች ተመድበው ለአንድ ዓመትና ከዚያ በላይ ሲያገለግሉ ላሳዩት ከፍተኛ የስራ አፈፃፀም ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እንዲሁም በእረፍት ሰዓታቸው የግል ስራቸውን ቢያከናውኑ ሊያገኙ የሚችሉትን ከፍተኛ የሆነ ገቢ ግንዛቤ ውስጥ ሳያስገባ ቢያንስ ላበረከቱት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደ ማካካሻ እንዲሆን ታሳቢ ተደርጎ ጉዳዩ በማኔጅመንት ቀርቦ ውሳኔ ከተሰጠበት በኋላ ክፍያው የተፈፀመ መሆኑን፣
- ለወደፊቱ ለእንደዚህ ዓይነቱ አገልግሎት መምህራንና ሰራተኞች በእረፍት ጊዚያቸው ሲያገለግሉ ሊከፈል የሚገባውን ተመጣጣኝ ክፍያ መፈፀም የምንችልበትን መንገድ ከሚመለከተው የመንግስት አካል ጠይቀው የሚከፍሉ መሆኑን ገልጸው በቀጣይ የሚመለከተውም የመንግስት አካል በጉዳዩ ላይ ቀጥተኛ ምላሽ ባይሰጥ በስራ አፈፃፀማቸው ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚፈጥር መሆኑን፣ በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

2.1.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

የሥራው አስፈላጊነት ቢታመንበት እንኳ የመምህራንን ሁኔታው ተጣርቶ መንግሥት በክሬዲት ሀወር ባወጣው ተመን፣ የአስተዳደር ሠራተኞችን ደግሞ ከሚመለከተው አካል በማስፈቀድ መክፈል ይገባ ነበር፡፡ ስለሆነም የተሰጠው ምላሽ አጥጋቢ ባለመሆኑ በማሻሻያ ሀሣቡ መሠረት እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል፡፡

2.6 የኮንትራት ሰራተኞች ክፍያ፣

2.6.1 ግኝት፣

ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ህዳር 18 ቀን 2005 ዓ.ም በቁጥር መ80-839/1 በተፃፈ ደብዳቤ ዘላቂነት ባለውና በተመደበ የሥራ መደብ ላይ በኮንትራት (በጊዜያዊነት) በፌዴራል የመንግሥት መ/ቤቶች ተቀጥረው ያልተቋረጠ አገልግሎት ሲሰጡ የቆዩ ሠራተኞች በቋሚነት እንዲመደቡ፣ በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ባልተመደበና ዘላቂነት በሌለው የሥራ መደብ ላይ በኮንትራት /በጊዜያዊነት/ ተቀጥረው የነበሩ ሠራተኞች ቅጥር እንዲቋረጥ ሆኖ በአስቸኳይ መሰናበት እንዳለባቸው፣ ይህ መመሪያ ለአንድ ጊዜ አፈፃፀም ብቻ የሚያገለግል ሲሆን ከየካቲት 30/2005 ዓ.ም በኋላ ተግባራዊ ማድረግ እንደማይቻል እንዲሁም እጅግ አስፈላጊ ለሆነና ለአጭር ጊዜ ብቻ የኮንትራት/ጊዜያዊ ቅጥር መፈጸም አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ ጥያቄው በመጀመሪያ ለሲቪል ሠርቪስ ሚኒስቴር ቀርቦ ተቀባይነት ማግኘት እንዳለበት መመሪያ መተላለፉ ይታወቃል፡፡

ይሁን እንጂ በዩኒቨርሲቲው የሚገኙ የኮንትራት/ጊዜያዊ ሠራተኞች በቋሚ የሥራ መደብ ላይ በቋሚነት ሳይመደቡ ወይም ዘላቂነት ከሌለው የሥራ መደብ ላይ ሳይሰናበቱ እና ዩኒቨርሲቲው በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል ጠይቆ ሳያስፈቅድ በበጀት ዓመቱ፣ ለኤሌክትሪክ፣ ለቧንቧ፣ ለግቢ ጸጥታ፣ ለካፍቴሪያ፣ ለዉሃ ኦፕሬተር እና ለወጥ ቤት ሠራተኞች በበጀት ዓመቱ በሂሳብ መደብ 6114 (የቀን ሠራተኞች ምንዳ) በድምሩ ብር 1,803,491.00 የተከፈለ መሆኑ ታውቋል፡፡

2.6.2 ሥጋት፣

- ደንብና መመሪያን ያልተከተለ ክፍያ መፈጸም ለገንዘብ ብክነት ከመዳረጉም ባሻገር ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡

2.6.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- ለወደፊቱ ክፍያው በመንግስት መመሪያ መሰረት ተፈፃሚ እንዲሆን ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ሊደርግ ይገባል፡፡

2.6.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

የሥራ አመራሩ፣

- የቴክኒክ ባለሞያዎችን በተመለከተ በተደጋጋሚ ጊዜ በቋሚነት ቅጥር ለመፈፀም ማስታወቂያ ቢወጣም በፐብሊክ ሰርቪስ ሚኒስቴር ለቦታዎቹ የተፈቀደው ደመወዝ በአሁኑ ወቅት ገበያው ለባለሞያዎቹ ከሚከፍለው በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ በቅጥር ለመሸፈን አለመቻሉን፣ ይህንንም ችግር በጊዜያዊነት ለመቅረፍ ተቋሙ የ24 ሰዓት አገልግሎት የሚሰጥ በመሆኑ ባለሞያዎችን በቀን ሰራተኛ ቅጥር ፈፅሞ ስራዎቹን በማሸፈን ላይ እንደሚገኝ፣ በቀጣይም በጉዳዩ ላይ ከፐብሊክ ሰርቪስ ጋር ተወያይተው መፍትሄ እንዲሰጣቸው የሚያደርጉ መሆኑን፣
- በተማሪዎች ምግብ ቤት የወጥ ቤት ሰራተኞች በተደጋጋሚ ጊዜ በቋሚነት ቅጥር ለመፈፀም ማስታወቂያ ቢወጣም በፐብሊክ ሰርቪስ ሚኒስቴር ለቦታዎቹ የተፈቀደው ደመወዝ እና የሚጠይቀው ተፈላጊ የትምህርትና የስራ ልምድ በአሁኑ ወቅት ገበያው ለባለሞያዎቹ ከሚከፍለው በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ በቅጥር ለመሸፈን አለመቻሉን፣ ይህም ሁኔታ ችግር ውስጥ ቢከታቸውም አገልግሎቱ ለተማሪዎች የምግብ አገልግሎት መስጠት በመሆኑ እና አገልግሎቱም ለሰዓት መቋረጥ የማይችል ስለሆነ ይህንን ችግር ለመቅረፍ ሰራተኞችን በቀን ሰራተኝነት ለመቅጠርና አገልግሎቱን ለመስጠት የተገደዱ መሆኑን፣ በቀጣይም በጉዳዩ ላይ ከፐብሊክ ሰርቪስ ሚኒስቴር ጋር ተወያይተው መፍትሄ እንዲሰጣቸው የሚያደርጉ መሆኑን፣

ለሥራ አመራር ደብዳቤ በላኩት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

2.9 ለማገዶ እንጨት ግዥ ያላግባብ የተከፈለ ሂሳብ፣

2.9.1 ግኝት፣

ዩኒቨርሲቲው ለተማሪዎች ምግብ ማብሰያ አገልግሎት የሚውል የማገዶ እንጨት ለመግዛት ያወጣውን የጨረታ ሂደት ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በበጀት ዓመቱ አንድ ሜትር ክዩብ የማገዶ እንጨት በብር 580.00 ለማቅረብ ብርሃኑ ሄኖክ

ጠቅላላ ኮንስትራክሽን ድርጅት ጨረታውን ተወዳድሮ ያሸነፈ እና ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ የሚሆን ውል በ11/02/09 የፈረመ እንዲሁም በዕለቱ 30% ቅድሚያ ክፍያ እንዲሰጠው የጠየቀ ቢሆንም ግልጽ ባልሆነ ምክንያት መኮንን መርኔ ወ/መድህን የአጠና ድርጅት የማገዶ እንጨቱን እንዲያቀርብ በመደረጉ፣

- በ26/03/09 በሞ/19 ገቢ ለተደረገ የማገዶ እንጫት በቀን 27/03/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 457471 የአንዱ ሜትር ክዩብ ማገዶ እንጨት በብር 800.00 ሂሳብ፣ በድምሩ ብር 374,440.00 (ብር 800.00*468.05 ሜ/ኩ) በመከፈሉ ያለአግባብ በብልጫ /በልዩነት/ የብር 102,971.00 (/ብር 800.00*468.05 ሜ/ኩ/ — /ብር 580.00*468.05 ሜ/ኩ/) ግዥ፣
- በ06/03/09 በሞ/19 ቁጥር 13625 ገቢ ለተደረገ የማገዶ እንጨት በቀን 08/03/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 457354 የአንድ ሜትር ክዩብ ማገዶ እንጨት በብር 800.00 ሂሳብ፣ በድምሩ ብር 414,902.40 (ብር 800.00*518.628 ሜ/ኩ) ለመኮንን መርኔ ወ/መድህን የአጠና ድርጅት በመከፈሉ ያለአግባብ በብልጫ /በልዩነት/ የብር 114,098.16 (/ብር 800.00*518.628 ሜ/ኩ/ — /ብር 580.00*518.628 ሜ/ኩ/) ግዥ፣
- በ23/02/09 በሞ/19 ቁጥር 13618 ገቢ ለተደረገ የማገዶ እንጨት በቀን 25/02/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 457209 የአንድ ሜትር ክዩብ ማገዶ እንጨት በብር 800.00 ሂሳብ፣ በድምሩ ብር ለመኮንን መርኔ ወ/መድህን የአጠና ድርጅት 414,208.80 (ብር 800.00*517.761 ሜ/ኩ) በመከፈሉ ያለአግባብ በብልጫ /በልዩነት/ የብር 113,907.42 (/ብር 800.00*517.761 ሜ/ኩ/ — /ብር 580.00*517.761.ሜ/ኩ/) ግዥ፣

በድምሩ የብር 330,976.58 ግዥ ያለአግባብ በብልጫ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

2.9.2 ስጋት፣

- ደንብና መመሪያን ተግባራዊ ያላደረገ አሰራር የመንግስትን ሀብት ለብክነትና ለምዝበራ ሊጋለጥ ይችላል፡፡ ተጠያቂነትንም ያስከትላል፡፡

2.9.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- አሠራሩ የግዥ ሂደቱን ተዓማኒነት የሚያሳንስ በመሆኑ ጉዳዩ ተጣርቶ እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

- ለወደፊቱም ማንኛውም ግዥ መንግሥትን /ዩኒቨርሲቲውን/ ተጠቃሚ የሚያደርግና የመንግስትን አላስፈላጊ ወጪ የሚቀንስ ግልጽ የሆነ አሰራር መከተል ይኖርበታል፡፡

2.9.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

የሥራ አመራሩ፣

- በ2008 በጀት ዓመት የነበረው የማገዶ እንጨት ውል ከመኮንን መረኔ ወ/መድህን የአጣና አቅራቢ ድርጅት ጋር ሲሆን የ2009 በጀት ዓመት የጨረታ ሂደት ባለመጠናቀቁ እና ለተማሪዎች ምግብ ማብሰያ ባለመኖሩና አዲሱ ጨረታ ውል ተፈርሞ በአግባቡ የደረቀ እንጨት የሚቀርብበትን ጊዜ በግዥ ክፍሉ ታሳቢ በማድረግ 04/02/2009 ዓ/ም ተጨማሪ የ25% የማገዶ እንጨት እንዲያቀርብ በአስተዳደርና ልማት ምክትል ፕሬዝዳንት ተፈቅዶ ለአቅራቢው ትዕዛዝ የተሰጠበት መሆኑን፣ የዚህ አይነቱ ውሳኔ ላይ እንዲደርሱ ያስገደዳቸው በማገዶ እንጨት ያለመኖር ችግር ቢፈጠር ሊከሰት የሚችለውን ከፍተኛ አደጋ (የበሰለ የተማሪዎች ምግብ በወቅቱ ያለማድረስ) ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ካለው ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት የተፈፀመ ግዥ እንጂ ሆን ተብሎ የመንግስትንና የህዝብን ገንዘብ ለብክነት ለመዳረግ የተሰራ አለመሆኑን፣ በተጨማሪም የአቅርቦት ግዥው ይህንኑ መሰረት አድርጎ በቀረቡት ሰነዶች መነሻነት የተፈፀመ መሆኑን ገልጸው ለወደፊቱ የውል መነሻ እና መጨረሻ ጊዜን መሰረት አድርገው ግዥ የሚፈጽሙ መሆኑን፣ በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

2.9.4 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

የቀድሞው አቅራቢ 25%ቱን እንዲያቀርብ ትዕዛዝ በተሰጠው (04/02/2009) በሳምንቱ (11/02/2009) ሌላ ውል መገባቱ እና ውሉ ከተገባ በኋላም አዲሱን ውል ተፈጻሚ ከማድረግ ይልቅ የቀድሞው አቅራቢ እንዲያቀርብ ማድረጉ የግዥውን ተዓማኒነት ያሳንሳል፡፡ ስለሆነም በማሻሻያ ሀሳቡ መሠረት እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

2.10 <u>ያለምንም ውድድር የተከናወነ ቀጥታ ግዥ፣</u>

2.10.1 <u>ግኝት</u>፣

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ምዕራፍ-6 አንቀጽ-52 ተራቁጥር አንድ ለይ መንግስት መ/ቤቶች ከአንድ አቅራቢ ግዥ

መፈጸም የሚችሉት በፍደል-ሀ.ዕቃው፤ ግንባታ ዘርፍ ሥራው፤የምክር ወይም ተፈላጊው ሌላ አገልግሎት የሚገኘው ከአንድ ዕጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

በዚሁ መሰረት ዩንቨርሲቲው የመንግሥት ሀብት በአግባብና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ አስፈላጊ የሆነ ጨረታ በማውጣት ድርጅቶችን በጨረታ ጋብዞ በማውዳድር ዝቅተኛ ዋጋ አቅራቢ መምረጡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- በቀን 16/03/09 በባንክ ወጪ ማስመሰከሪያ ቁጥር 0817050 ለግቢ ዉስጥ የፍሳሽ ማስወገጃ/የሳኒቴሪ ሥራዎች ለታምራት አብዮትና ቡልቲ ኮንስትራክሽን ብር 190,850.19፤
- በቀን 12/03/09 በባንክ ወጪ ማስመሰከሪያ ቁጥር 0817047 ለግቢ ዉስጥ የፍሳሽ ማስወገጃ/የሳኒቴሪ ሥራዎች ለታምራት አብዮትና ቡልቲ ኮንስትራክሽን ብር 79,486.85፣
- በቀን 04/02/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0817037 የኤለክትሪክ መስመር ዝርጋታ ለዮሴፍ አረጋዉ ብዛዉ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ ብር 213,879.99፤
- በቀን 03/01/09 በባንክ ወጪ ማስመሰከሪያ ቁጥር 456800 Floor Paint Floor Epoxy ሥራ ለተሰራበት ከቃሊቲ ኮንስትራክሽን ዕቃዎች ፋብሪካ ብር 1,414,137.75፣

በድምሩ የብር 1,898,354.78 ግዥ ያለምንም ውድድር በቀጥታ ግዥ የተፈፀመ መሆኑን በኦዲት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

2.10.2 <u>ስጋት</u>፣

- መንግሥት ከዋጋና ከጥራት አኳያ ሊያገኝ የሚችለውን ጥቅም ሊያጣ ይችላል፡፡ ፡
- ግዥዎች በቀጥታ ከተወሰነ አቅራቢዎች ብቻ የሚከናወን ከሆነ ለሚከፈለው ክፍያ ጥራትና ብቃት ያለው ተመጣጣኝ የሆነ ዕቃ ወይም አገልግሎት ላይገኝ ይችላል፡፡
- ማንኛውም ግዥ በደንብና መመርያው መሰረት የማይከናወን ከሆነ የመንግስት ሀብት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

2.10.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፣

- ግዥዎች በግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ እና ስለአፈጻጸሙ በወጣው ደንብና መመሪያ መሰረት እንዲከናወኑ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.10.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የሥራ አመራሩ፣

- የተለያዩ የኤሌክትሪክ መስመር፡ የፍሳሽ ማስወገጃ መስመሮች በዩኒቨርሲቲው ህንፃዎች እና የተለያዩ ቦታዎች ላይ በአግባቡ ተዘርግተው የነበሩ ባለመሆናቸው ስራዎቹን ቀደም ሲል ከ2006 ዓ/ም ጀምሮ ተለይተው ከድሬዳዋ አስተዳደር ጥቃቅንና አነስተኛ ጋር በመነጋገር ጥሩ አፈፃፀም ያላቸውን ጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት ጠይቀን በተሰጠን መረጃ መሰረት ለተለያዩ በጥቃቅን ለተደራጁ ማህበራት ከMH አማካሪ ድርጅት በቀረበው የዋጋ ግምት መሰረት ስራዎቹን እንዲሰሩ ያደረጉ መሆኑን ጠቅሰው ለወደፊቱ የተሰጣቸውን አቅጣጫ መሰራት አድርገው የሚሠሩ መሆኑን የገለጹ ሲሆን፣
- የቃሊቲ ኮንስትራክሽንን በተመለከተ ደግሞ የመከላከያ ድርጅት እህት ኩባኒያ የሆነው ከቃሊቲ ኮንስትራክሽን አቅራቢ ድርጅት የቤተ ሙከራ ወለል የተሰራበት በ2008 ዓ/ም ለቤተ ሙከራ ግብዓት የሚሆኑ አቅርቦቶች በቀጥታ እንዲፈፅሙ ከግዥ ኤጀንሲ ጠይቀው ተፈቅዶላቸው አብዛኛውን የቤተ ሙከራ ግብዓት አቅርበው ለFloor Paint Floor Epoxy ስራ የሚሆን ግብዓት በወቅቱ ባለመቅረቡ ዘግይቶ የተሰራ መሆኑን በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

2.10.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

የቃሊቲ ኮንስትራክሽንን በተመለከተ በምላሹ በተጠቀሰው መሠረት ለመፈቀዱ የቀረበ ማስረጃ ስለሌለ በማሻሻያ ሀሳቡ መሠረት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

2.11 <u>በጨረታ መፈጸም ሲገባ ተከፋፍሎ በፕሮፎማ የተፈጸም ግዥ፣</u>

2.11.1 <u>ግኝት፣</u>

- ሰኔ 2002 በወጣው የግዥ መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 15.3 እና 15.4 በአዋጁ እና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግሥት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልጽ ጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው እና ከግልጽ ጨረታ ውጭ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈጸም የሚችሉት በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተገለጹት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ እንደሆነ ተጠቅሷል፡፡
- በተጨማሪም ከታህሳስ 12/2008 ጀምሮ ሥራ እንዲውል በተሸሻለው የፌዴራል መንግስት የግዥ መመሪያ አንቀፅ 24.2 መሰረት በፕሮፍርማ የሚገዛ ዕቃ ግዥ

ጣሪያ እስከ ብር 200,000.00 እንደሆነ፣ በዚሁ መመሪያ አንቀጽ ቁጥር 24.12 ላይ ደግሞ የመንግስት መ/ቤቶች በአንድነት ሊፈፀሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ከፋፍለው መግዛት እንደሌለባቸው ተገልጿል፡፡

ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲው የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ግዥዎች በአዋጁ እና በመመሪያዉ መሰረት መፈፀማቸውን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፤ ለመዝናኛ ክበብ አገልግሎት የሚውሉ የብር 397,600.01 ጠረጴዛዎች፣ ወንበሮችና ሶፋዎችን በጨረታ የግዥ ዘዴ መግዛት ሲገባ ግዥዉን በብር 143,640.01፣ ብር 58,320.00 እና ብር 195,640.00 በመከፋፈል በተመሳሳይ ቀን (በ18/02/09) ሶስት የዋጋ ማቅረቢያ በመሰብሰብ በቀን 23/03/09 በJV554235 ከዋሪት ሙሉ ጥላ ኢንተርናሽናል ኃ.የተ.የግል ኩባንያ በሁለት ጊዜ በብር 143,640.1 እና በብር 58,320.00፣ በድምሩ በብር 201,960.01፣ ከSUNJUN BO FURNITURES PRODUCTION ደግሞ በብር 195,640.00፣ በጠቅላላ ድምሩ የብር **397,600.01** ግዥ 3 ቦታ ተከፋፍሎ ግዥው በዋጋ ማወዳደሪያ መፈጸሙ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

2.11.2 ስጋት፣

- አስፈላጊነታቸው በመንግስት ታምኖበት የወጡ አዋጆች ደንቦችና መመሪያዎችን መተላለፍ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡
- አሠራሩ መንግስት ከጥቅል ግዥ ሊያገኝ የሚችለውን ጥቅም ያሳጣዋል፡፡
- መመሪያን ያልተከተለ የግዥ ሥርዓት ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

2.11.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- ኢንስቲትዩቱ የሚፈፅማቸውን በግልጽ ጨረታ በጥቅል ሊገዙ የሚችሉትን ግዥዎች በእቅድ ይዞ በመመሪያው መሠረት እንዲገዙ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም የዚህ አይነት አሰራር እንዳይከሰት ተገቢው ጥንቃቄ ሊያደረግ ይገባል፡፡

2.11.4 የሥር አመራሩ ምለሽ፤

የሥራ አመራሩ ለመምህራንና ለሰራተኞች መዝናኛ ክበብ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በበቂ ሁኔታ የተደራጀ ባለመኖሩ ተደጋጋሚ ቅሬታ በማስነሳቱና የመልካም አስተዳደር ችግር ጥያቄ ሆኖ በመቅረቡ ዩኒቨርሲቲው ይህን አገልግሎት ለማቅረብ ለዚሁ አገልግሎት የሚውል ህንፃ በማሳደስና ሊሟሉ የሚገቡ መቀመጫና ጠረጴዛዎች በማስፈለጉ በአስቸኳይ መልስ እንዲሰጥ በዩኒቨርሲቲው ቦርድ አቅጣጫ

ስለተቀመጠ ዩኒቨርሲቲው በኢንስቲትዮትቱ በኩል በአስቸኳይ በግዥ እንዲሟላ ባደረገው መሰረት የኢንስቲትዮትቱ ማናጅመንት በውስን ጨረታ እንዲገዛ የወሰነ ቢሆንም፤ ድርጅቶቹ ጨረታ ሰነዱን በሚጋበዙበት ወቅት እቃውን ለማቅረብ ከ90-120 ቀናት እንደሚወስድና ከውጭ ለማስመጣት ጊዜ እንደሚፈልጉ ስለገለፁ የግዥ ቡድን ይህንን ለኢንስቲትዩቱ በማሳወቃቸው የዩኒቨርሲቲው ማናጅመንት አባል የሆኑት ሳይንቲፊክ ዳይሬክተር ከዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ጋር በመወያየት ቡድኑ በዋጋ ማቅረቢያ ዘዴ ገዝቶ እንዲመጣ ትዕዛዝ በማስተላለፍቸው በዋጋ ማቅረቢያ ሊገዛ መቻሉን ጠቅሰው ህግ ለመጣስ ሳይሆን ግዥውን በዋጋ ማቅረቢያ በየዘርፋቸው ተለይቶ የተጠየቀና አብዛኞቹን አንድ ድርጅት ያሸነፈ በመሆኑ መሆኑን በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

2.11.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

በምላሹ ላይ ትዕዛዝ የተላለፈበት ደብዳቤ የተባለው ከምለሹ ጋ ያልቀረበ ቢሆን ቀርቦ ቢሆን እንኳ የግዥ መመሪያው በኃላፊዎች ትዕዛዝ ሊሻር ስለማይችል ለወደፊቱ በማሻሻያ ሀሳቡ መሠረት መሠራት አለበት፡፡

2.14 <u>ከቀረበለት ማስረጃ በመብለጥ የተከፈለ ሂሳብ፣</u>

2.14.1 <u>ግኝት፣</u>

የዩኒቨርሲቲው ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ክፍያዎች ከመፈጸማቸው በፊት በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 9 ላይ የተጠቀሱ ጥንቃቄዎች መደረጋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ለቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩቱ ማስፋፊያ ለግንባታ ለሚሆን መሬት ለተፈናቃዮች ካሳ ክፍያ በቀን 30/10/09 በወጪ ማዘዣ ቁጥር 353594 በሂሳብ መደብ 6416 ብር 34,519,384.53 ወጪ ተደርጎ ወደ ድሬ ዳዋ ከንቲባ ጽህፈት ቤት የባንክ ሂሳብ ገቢ የተደረገ ሲሆን፣ ግምቱ የተደረገበትና ለክፍያ የቀረበው ሰነድ የብር 34,469,487.49 በመሆኑ በልዩነት ብር 49,897.04 (34,519,384.53 - 34,469,487.49) ወደ ከንቲባ ጽህፈት ቤቱ የባንክ ሂሳብ ገቢ የተደረገ መሆኑ፣ ተረጋግጧል፡፡

2.14.2 <u>ሥጋት፣</u>

- በልዩነት ወደ ከንቲባ ጽ/ቤቱ የተላለፈው ገንዘብ ሥራ ላይ ባይውል ወደ መንግስት ካዝና ላይመለስ ይችላል፡፡

2.14.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- በልዩነት የተከፈለው ሂሳብ ተመላሽ መደረግ አለበት፡፡

2.14.4 <u>የሥራ አመራሩ ምለሽ፤</u>

የሥራ አመራሩ የተገለጸው የካሳ ክፍያ የተላለፈው ለድሬ ዳዋ አስተዳደር ከንቲባ ጽህፈት ቤት በመሆኑ ሙሉ ለሙሉ ለግለሰቦቹ የካሳው ክፍያው ሲፈጸም ቀሪውን ብር ተመላሽ እንዲሆን የሚያደርጉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

2.16 <u>አስቀድሞ በጀት ባልተያዘበት የወጪ ሂሳብ መደብ</u>
<u>ከውስጥ ገቢ ለምግብ ግብዓት ግዥ የወጣ፣</u>

2.16.1 <u>ግኝት፣</u>

- የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 6 የመንግስት መ/ቤቶች በጀት ክፍያ የሚፈጸመው ወይም ወጪ የሚደረገው የተፈቀደ በጀት ሲኖር ብቻ መሆኑን ይገልጻል፡፡
- በተጨማሪም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 39/2006 አንቀጽ 5/4 በመንግስት ውሳኔ የተሰጠባቸው እንደ የተማሪዎችና የህሙማን የምግብ በጀት ተመን የመሳሰሉት ወጪዎች ከውስጥ ገቢ ከተመን በላይ መጠቀም እንደማይቻል ተገልጿል፡፡

ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው ከውስጥ ገቢ ሂሳብ ያወጣቸው ክፍያዎች በመመሪያው መሠረት የተፈጸሙ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ለተማሪዎች ምግብ የሚውል የምግብ ዘይት ከሀማሬሳ የምግብ ዘይት አክሲዮን ማህበር በቀን 14/10/09 በባንክ ማስመስከሪያ ቁጥር 458884 የተገዛበት ብር 129,690.00 እና በቀን 20/10/09 በባንክ ማስመስከሪያ ቁጥር 458898 የተገዛበት ብር 102,041.40፣ በድምሩ ብር 231,731.40 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 39/2006 ከሚያዘው ውጭ እና አስቀድሞ በተፈቀደ በጀት ሳይያዝ ከውስጥ ገቢ ሂሳብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

2.16.2 <u>ሥጋት፣</u>

- በጀት ሳይያዝለት ወጪ መፈጸም እና ከውስጥ ገቢ የሚወጣውን ወጪ መመሪያ አለመከተል በዩኒቨርሲቲው የበጀት አጠቃቀም ላይ አሉታዊ ተጽኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡ ለብልሹ አሠራርም መንስኤ ሊሆን ይችላል፡፡

2.16.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፣

- ዩኒቨርሲቲው ማናቸውንም ክፍያ ሲፈጽም የመንግስት ደንብና መመሪያን መሰረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ከመመሪያ ውጪ ክፍያ መፈጸምም የህግ ጥሰት በመሆኑ ለወደፊቱ መቆም ያለበት ሲሆን የግድ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የሚመለከተውን አካል ጠይቆ በማስፈቀድ መፈጸም አለበት፡፡

2.16.4 <u>የሥራ አመራሩ ምለሽ</u>፤

የሥራ አመራሩ ክረምት በግል የሚማሩ ተማሪዎች የተጠቀሙት የምግብ ፍጆታ ቀድመው ለዩኒቨርሲቲው ክፍያ ስለሚፈጽሙ በጀት በሚታወጅበት ወቅት ባለመታወጁ የተከሰተ ሲሆን ለወደፊቱ ማስተካከያ የሚያደርጉበት መሆኑን በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

2.17 <u>በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ</u>፤

2.17.1 <u>ግኝት</u>፣

ስለፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 ክፍል ሦስት አንቀጽ 12 የመንግሥት ገንዘብ ክፍያ ሊፈጸም ወይም ወጪ ሊደረግ የሚችለው የተፈቀደ በጀት ሲኖር ብቻ ነው ይላል፡፡

ይሁን እንጂ ከባድሮ በክሪ የኤሌክትሪክ እና የኤሌክትሮኒክ ዕቃዎች የተገዙ የብር 1,868,905.24 ዕቃዎች ገቢ የተደረጉት በቀን 21/10/08 (2008 በጀት ዓመት) ቢሆንም ክፍያው በ2009 በጀት ዓመት ተፈጽሞ ወጪው በቀን 19/12/08 ዓ.ም (2009 በጀት ዓመት) በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 456752 የተመዘገበ በመሆኑ በ2008 በጀት ዓመት የተገዛውና ገቢ የተደረገው ዕቃ በ2009 በጀት ዓመት በወጪ የተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡

2.17.2 <u>ስጋት</u>፣

- ደንብና መመሪያ ተፈጻሚ እንዳይሆን ከማድረጉም በተጨማሪ ያለፈው በጀት (2008) የወጪ ሂሳብ ዝቅ እንዲልና የ2009 የበጀት ዓመት ሂሳብ ከፍ ሊያደርገው ይችላል፡፡

2.17.3 <u>የማሻሻ ሀሳብ</u>፣

- ክፍያ በአዋጁ መሠረት የበጀት ዓመቱን ጠብቆ ማከናወን እና መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

2.17.4 <u>የሥራ አመራሩ ምለሽ፤</u>

- የሥራ አመራሩ ንብረቱ ገቢ የተደረገው ሰኔ 2008 ዓ.ም ቢሆንም በወቅቱ ክፍያ መፈጸም ባለመቻሉና ንብረቱም አላቂ ዕቃ በመሆኑ በ2008 በጀት ዓመት ክፍያው አለመፈጸሙን ጠቅሰው ዕቃው በ2009 በጀት ዓመት አገልግሎት ላይ እንዲውል የተደረገና ክፍያውም በ2009 በጀት ዓመት የተፈጸመ መሆኑን፣ ለወደፊቱ አቅራቢዎች በተባለው ጊዜ እንዲያቀርቡ እና የበጀት አጠቃቀማቸውን በእቅዱ ላይ በተቀመጠው መሰረት እንዲሆን ክትትል የሚያደርጉ መሆኑን በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

2.18 <u>የዩኒቨርሲቲውን ከፌ ለማይጠቀሙ ተማሪዎች /None caffe/ በማነስ የተከፈለ ሂሳብ፣</u>

2.18.1 <u>ግኝት፣</u>

በፈቃደኝነት የምግብ አገልግሎት/የወጪ መጋራት/ ወደ ገንዘብ እንዲቀየርላቸው የፈለጉ ተማሪዎች ክፍያ ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በሂሳብ መደብ 6216 የወጪ መጋራት ለአንድ ተማሪዎች በቀን ብር 15.00፣ ለ30 ቀን ብር 450.00 (15.00*30) መሆን ሲገባው ለባንክ አገልግሎት ክፍያ በማለት ብር 3.00 ተቀንሶ ብር 447.00 የተከፈላቸው በመሆኑ፣

- በቀን 22/05/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 457397 ከጥር ወር/2009 ከ3,252 ተማሪዎች ላይ በድምሩ ብር 9,756.00 (3252*3.00) የተቀነሰባቸው መሆኑ፣
- በቀን 14/02/09 በባንክ የወጪማስመስከሪያ ቁጥር 457039 ከ3021 ተማሪዎች ላይ ብር 9,063.00 የተቀነሰባቸው መሆኑ፣
- በቀን 28/0209 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 457226 የጥቅምት ወር/2009 ከ3050 ተማሪዎች ላይ በድምሩ ብር 9,150.00 (3050*3.00) የተቀነሰባቸው መሆኑ፣

- በቀን 22/02/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 457201 የጥር ወር/2009 ከ839 ተማሪዎች ላይ በድምሩ ብር 2,517.00 (839*3) የተቀነሰባቸው መሆኑ፣
- በቀን 24/06/09 በባንክ ወጪማስመስከሪያ ቁጥር 458167 የጥር ወር/2009 ወጪ ከ3129 ተማሪዎች ላይ ብር 9,387.00 (3129*3)፣

በጠቅላላ ድምሩ ብር 39,873.00 በመንግስት ለተማሪዎቹ ከተፈቀደላቸው ከወርዊ የምግብ ክፍያቸው ላይ ለባንክ አገልግሎት ክፍያ በማለት የተቀነሰባቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

2.18.2 ስጋት፣

- በተማሪዎቹ ላይ ተጽዕኖ ሊፈጠር ይችላል፡፡
- ለመልካም አስተዳደር ችግር መንስኤ ሊሆን ይችላል፡፡

2.18.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- የባንክ አገልግሎት ክፍያው በሌላ ዘዴ ተሸፍኖ ለተማሪዎቹ በመንግስት የተፈቀደላቸው ሂሳብ ተሟልቶ የሚከፈልበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

2.18.4 የሥራ አመራሩ ምለሽ፤

- የሥራ አመራሩ ዩኒቨርሲቲው የተማሪዎች የምግብ ክፍያ /Non café/ በባንክ በኩል እንዲፈፀም ተማሪዎች ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት የአገልግሎት ክፍያው እንዲቀነሰስባቸው በመግለፃቸው ባንኩና ዩኒቨርሲቲው የተስማሙበት መሆኑን ለመረዳት የቻሉ መሆኑን ጠቅሰው ጉዳዩን በሚገባ አጣርተው መስተካከል ካለበት ከሚመለከተው አካላት ጋር ወደፊት ተወያይተው የሚያስተካክሉ መሆኑን ለሥራ አመራር ደብዳቤው በላኩት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

2.21 ለአንድ ኮንትራክተር የተለያዩ ተደራራቢ የግንባታ ሥራዎች የተሰጡ ስለመሆኑ፣

2.21.1 ግኝት፣

ዩኒቨርሲቲዉ የሚያስገነባቸዉ የተለያዩ የግንባታ ፕሮጀክቶች የዉል አስተዳደር፣ የቁጥጥር ሥርዓትና የሥራ አፈጻጸም ሁኔታ ለማጣራት በናሙና ኦዲት ሲደረግ፣ FE Construction የተባለ ተቋራጭ ቀድሞ የወሰዳቸውን ግንባታዎች በተሰጠዉ የጊዜ ገደብ ውስጥ አጠናቅቆ ሳያስረክብ ሌሎች የተለያዩ የግንባታ ሥራዎች በተደራራቢ የተሰጡት በመሆኑ ሥራዎቹ እየተጓተቱ ሲሆን በዚህም ምክንያት የካቲት/2007 እና መጋቢት/08 መጠናቀቅ የነበረባቸው ግንባታዎች እስከ የካቲት 30/2009 ዓ.ም ድረስ ያልተጠናቀቁና የውል ማራዘሚያ ጊዜ እየተጠየቀባቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

ዝርዝሩም፣

ተ.ቁ	የፕሮጀክቱ ዓይነት	መነሻ የውል ዋጋ	ውል የተገባበት ቀን	ለሥራው የተሰጠ ጊዜ በቀናት	ውሉ የሚያበቃበት (ግንባታው የሚጠናቀቅበት) ቀን	ግንባታው የተጠናቀቀበት ቀን
1	መማሪያ ክፍሎች	84,249,832.13	June 20,2014	270	መጋቢት 8/2007	
2	ዋና መጋዘን (2)	8,673,369.30	June 20,2014	180	የካቲት 30/2007	
3	ሴሚናር ህንጻ	12,361,994.32	Dec. 22/2015	90	መጋቢት12/2008	02/03/09
4	ላይብረሪ	11,477,221.48	Dec. 22/2015	90	መጋቢት12/2008	05/11/08
5	የዋናዉ በርና የአጥር ግንባታ	51,829,735.44	Oct 8 2008 EC	170	መጋቢት 28/2008	

2.21.2 ስጋት፣

- የዉሉ መደራረብ በኮንትራክተሩ ላይ ከፍተኛ የስራ ጫና ስለሚያሳድርበት ስራዉን በተሰጠዉ የጊዜ ገደብ ካለማጠናቀቁም አልፎ በስራ ጥራት ላይም አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡
- ፕሮጀክቱ በተጓተተ ልክ የዕቃዎች ዋጋ እየጨመረ በዋጋ ማስተካከያ ምክንያት ዩኒቨርሲቲውን አላግባብ የሆነ ወጪ ሊያስወጣ ይችላል፡፡
- በዉል መደራረብ ምክንያት ለሚፈጠረዉ የስራ አፈጻጸም መጓተትን ተከትሎ የሚመጣ የዉል ማራዘሚያና የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ ተጠያቅነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

2.21.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- ፕሮጀክቶቹ ቶሎ ተጠናቀው ለአገልግሎት ክፍት እንዲሆኑ ወይም ተፈላጊዉን አገልግሎት መስጠት እንዲጀምሩ ጥብቅ ሆነ ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.21.4 የሥራ አመራሩ ምለሽ፤

የሥራ አመራሩ፣

- በተጠቀሱት ፕሮጀክቶች ላይ በተለይም የመማሪያ ክፍል፣ የስፖርት ማዘውተሪያና የዋና መጋዘን በተመሳሳይ ጊዜ የተከናወኑ ውሎች ሲሆን ተቋራጩም ፕሮጀክቶቹን በሚፈለገው ጊዜ አስረክቦ ዩኒቨርሲቲው እየተጠቀመበት የሚገኝ ሲሆን በኦዲት ግኝት ላይ ሊሰፈር የቻለው ከአማካሪው

መቅረብ የሚጠበቅበት የርክክብ ሰነድ በመዘግየቱ መሆኑን፣ የዋና መጋዘን ሁለት ውለታም ዩኒቨርሲቲውን ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ በተመሳሳይ ዋጋ ኤጀንሲውን በማስፈቀድ ተከናውኖ አገልግሎት መስጠት ከጀመረ ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ ሲሆን የዚህም ፕሮጀክት የርክክብ ሰነድ ከአማካሪ ድርጅት ባለመቅረቡ በተደጋጋሚ በኦዲት ግኝትነት እየተመዘገበ እንደሚገኝ፣

- የሴሚናርና የላይብረሪ ግንባታም በተመሳሳይ ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ከጀመረ የቆየ ሲሆን ቢዘገይም የነዚህም ግንባታዎች የርክክብ ሰነድ ማስገባታቸውን፣ በተጨማሪም ፕሮጀክቶቹ ተጠናቀው በአገልግሎት ላይ መሆናቸውን በመስክ ጉብኝትም ማረጋገጥ የሚቻል ሲሆን ድርጅቱ ከያዛቸው ግንባታዎች በአሁኑ ወቅት ያልተጠናቀቀው የዋና በርና አጥር ብቻ ሲሆን ይህም በድርጅቱ ድክመት ሣይሆን በወሰን ማስከበርና በዲዛይን ክፍተት የተፈጠረ መሆኑ ከግንዛቤ እንዲገባ ጠቅሰው ዩኒቨርሲቲውም ክትትሉን በማጠናከር የተጠቀሰውን ፕሮጀክት ለማጠናከር በመስረት ላይ እንደሚገኝ፣

ለስራ አመራር ደብዳቤ በላኩት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

3. ተሰብሳቢ ሂሳብ፣

3.1 ግኝት፣

- የፌዴራል መንግስት ፋይናንስ አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 የቅድሚያ ክፍያ በተሰጠው በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ መወራረድ አለበት ይላል::
- በፌዴራል መንግስት ሂስብ አያያዝ እና አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 የሂሳብ አያያዝ አፈፃፀም ንዑስ ቁጥር 4 ተሰብሳቢ ሂሳብ (መ) ደግሞ ተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብለት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሰብ መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ይገልፃል::

ይሁን እንጅ የዩኒቨርሲቲው በተለያዩ የተሰብሳቢ ሂሳብ መደቦች ከተለያዩ ግለስቦች እና ድርጅቶች የሚሰበሰብ የመንግስት ገንዘብ በተስብሳቢ የሚታዩ ሂሳቦች መወራረድ ባለባቸው ወቅት እንደማይወራረዱና እየተንከባለሉ የሚሄዱ መሆኑንና በበጀት ዓመቱ በድምሩ ብር **46,589,112.78** በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ የታወቀ ሲሆን ይህም፣

- በተንጠልጣይ ሂሳብ መደብ 4201 የብር 793,526.70 ሂሳብ በተለያዩ ሰራተኞች ስም ያለና ሳይወራረድ ከ14 ቀን እስከ ሶስት ዓመት የቆየ መሆኑ፤
- በመንግስት ሰራተኞች የደመወዝ ብድር /ሂሳብ መደብ 4203/ ብር 3,325.00 በተለያዩ የዩንቨርሲቲው ሰራተኞች ስም ያለው የአንድ ወር የጊዜ ገደብ ብቻ ቢኖረውም ከሁለት ዓመት በላይ ሳይወራረድ የቆየ መሆኑ፣
- በግዥ ቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ መደብ 4211 የተያዘው ብር 48,586.40 በሰባት የስራ ቀናት ውስጥ መወራረድ እንደነበረበት መመሪያው ቢያዝም ለ2007 ዓ.ም ጀምሮ ሳይወራረድ የቆየ መሆኑ፣
- የግንባታ ሥራ ተቋራጮች ቅድሚያ ክፍያ /ሂሳብ መደብ 4251/ የተያዘው ብር 30,057,204.80 (የGIZ-IS ብር 25,112,475.60 + የሌሎች ብር 4,944,729.19) የግንባታ ሥራው ተጠናቆ እና ተቋርጦ እያለ የቅድሚያ ክፍያው በዩኒቨርሲቲው በግንባታ ስራ ላይ ከተሳተፉ የሥራ ተቋራጮች ያልተሰበሰበ መሆኑ፣
- ለዕቃ አቅራቢዎች የሚፈጸም የቅድሚያ ክፍያ /ሂሳብ መደብ 4253/ የተያዘው ብር 15,624,011.53 በተለያዩ ግለሰቦችና ድርጅቶች ስም ያለ ሲሆን አቅርቦቱ በተለያየ ምክንያት የቆመ በመሆኑ ሳይወራረድ ከአምስት ዓመት በላይ የቆየ መሆኑ፣
- በሌሎች /others 4274/ የተያዘ ብር 62,458.35 በተለያዩ የዩኒቨርሲቲው ሰራተኞች ስም ያለ ሲሆን መወራረድ ከነበረበት እስከ ሁለት ዓመት የዘገየ መሆኑ፣

በጠቅላላ ድምሩ የብር **46,589,112.78** ተሰብሳቢ ሂሳብ እርምጃ ያልተወሰደበትና እየተንከባለለ የመጣ ያልተወራረደ ሂሳብ መሆኑ ታውቋል፡፡

በተጨማሪም በሂሳብ መደብ 4251 ከተያው ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 30,057,204.80 ውስጥ በGIZ-IS ስም የተያዘው ብር 25,112,475.60 ዝርዝር ሁኔታ ሲጣራ፣

ዩንቨርሲቲው በGIZ-IS አስተባባሪነት በግቢው ውስጥ ለሚያስገነባው የፍሳሽ ውኃ ማጣሪያ ፕላንት ሥራ በቅድሚያ ክፍያ መልክ የከፈለዉና ወደ 2009 በጀት በዓመት የዞረዉ ጠቅላላ የብር 43,224,976.87 ሲሆን በ2009 በጀት ዓመት ብር 5,580,000.00 ተጨምሮለት በጠቅላላዉ ብር 48,804,976.87 የቅድሚያ ክፍያ በ4251 ሂሳብ ተይዞ የተሰጠው ሲሆን እስከ ሰኔ 30/2009 ፕሮጀክቶቹ በመጠናቀቃቸው የመያዣዣ ሂሳቡ /retention/ ለሥራ ተቋራጩ የተመለሰለት ቢሆንም ከጠቅላለው በ4251 በድርጅቱ ስም ተይዞ የነበረው የቅድሚያ ክፍያ ብር 48,804,976.87 ውስጥ ብር 23,692,501.26 ብቻ ተወራርዶ በወጪ

የተያዘ ሲሆን ብር 25,112,475.61 ሳይወራረድ/ከድርጅቱ ሳይሰበሰብ/ የፕሮጀክቱ ሥራ የተጠናቀቀ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

(ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 1 ተመልክቷል፡፡)

3.2 ሥጋት፣

- ተሰብሳቢ ሂሳብ በወቅቱ ካልተወራረደ የመንግስት ገንዘብ ሳይሰበሰብ ባክኖ ሊቀር የሚችልበት አጋጣሚ ሊኖር ይችላል፡፡ በተጨማሪም ሂሳቡ በሂሳብ መግለጫ ላይ በየዓመቱ በተደጋጋሚ እንዲታይ ከማድረጉም ሌላ የዩኒቨርሲቲው በጀት አላግባብ እንዲቀነስ ያደርገዋል፡፡
- የGIZ-IS ተሰብሳቢ ሂሳብን በተመለከተ የቅድሚያ ክፍያው ስራው ከመጠናቀቁ በፊት ተሰብስቦ ማለቅ የነበረበት በመሆኑ ሥራው ከተጠናቀቀ በኃላ ቀሪው ብር ላይሰበሰብ ወይም ሰነድ ላይቀርብለት ይችላል፡፡ ህግና መመሪያው ባለመከበሩ ምክንያትም የመንግሥት ገንዘብ ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

3.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- ከላይ የተመለከተው ያልተወራረደው ተሰብሳቢ ሂሳብ መወራረድ አለበት፡፡
- ለወደፊቱም የቅድሚያ ክፍያ ሒሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ እና መሰብሰብ የሚገባቸው ከሚመለከታቸው አካላት ላይ ገቢ እንዲደረጉ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

3.4 የሥራ አመራሩ ምለሽ፤

የሥራ አመራሩ፣

- *ለመምህራንና ለሰራተኞች የተፈፀሙ የቅድመ ክፍያዎችን /4201/ የበጀት ዓመቱ ከተዘጋ በኋላ የሚታየውን ሂሳብ ብር 793,526.7 (ሰባት መቶ ዘጠና ሶስት ሺህ አምስት መቶ ሃያ ስድስት ብር ከ70/100) ውስጥ ብር 409,191.05 (አራት መቶ ዘጠኝ ሺህ አንድ መቶ ዘጠና አንድ ከ05/100) በአሁኑ ሰዓት ሰብስበው ገቢ ያደረጉ መሆኑን እና በተለይ ከምርምር ጋር ተያይዞ ለረጅም ጊዜ ያልተወራረዱትን ለሚመለከተው የበላይ አካል ውሳኔ እንዲሰጥበት ያስተላለፉ መሆኑን ገልጸው ሌሎች በዚህ መደብ በተሰብሳቢነት የሚታዩትን ሰብስበው ገቢ የሚደርጉ መሆኑን፣*
- *በ2003 ዓ/ም የተከፈለ የረጅም ጊዜ ብድር /4203/ የአንድ መምህር ስለሆነ የጉዳዩን አሳሳቢነት ተመልክተው በህግ ክፍላቸው በኩል አስፈላጊው ስራ እንዲሰራ ያስተላለፉ መሆኑን፣*

- በግዥ ሰራተኛ /4211/ የሚታየውን ሂሳብ ግለሰቡ በወቅቱ ተመላሽ ባለማድረጉ ለዩኒቨርሲቲው ህግ ክፍል ጉዳዩ ተሰጥቶ በአሁኑ ወቅት ጉዳዩ በፍ/ቤት እየታየ እንደሚገኝ እና በፍ/ቤቱ የሚተላለፈውን ውሳኔ መሰረት አድርገው የሚፈጽሙ መሆኑን፣
- በ/4251/ ከሚታየው ውስጥ ቀደም ሲል 13ቱ ዩኒቨርስቲዎች ሲመሰረቱ የግንባታ ስራቸውን ዩኒቨርስቲዎቹን ወክሎ እንዲያሰራ በትምህርት ሚኒስቴር ለGIZ- - IS ኃላፊነቱ የተሰጠ መሆኑን ጠቅሰው ከነዚህም ግንባታዎች ውስጥ አንዱ የቆሻሻ ውሃ ማጣሪያ ግንባታ አንዱ ሲሆን ለዚህም ግንባታ ማስፈፀሚያ የሚሆነውን ገንዘብ በቅድሚያ ከዩኒቨርስቲው ለ GIZ-IS በባንክ ገቢ የተደረገ ሲሆን ሂሳቡም የሚወራረደው GIZ-IS በሚያቀርበው ክፍያ የተፈፀመባቸው ሰነዶች በመሆኑ እነዚህ ሰነዶች ወቅቱን ጠብቀው ለዩኒቨርሲቲው ባለመቅረባቸው ሂሳቡ ሳይወራረድ ለረጅም ጊዜ የቆየ በመሆኑ በአሁኑ ወቅት በ GIZ-IS ስም የሚታየውን ተሰብሳቢ ሂሳብ ለማወራረድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተነጋግረው ክፍያ የተፈፀመባቸው ሰነዶች እንዲቀርቡ ጥረት እያደረጉ መሆኑን፣
- በአቅራቢዎች ስም በሂሳብ መደብ /4253/ የሚታየው ተሰብሳቢ ሂሳብ አቅራቢዎች የላብራቶሪ እቃዎች እና የምግብ ቤት ማሽነሪዎች ለመግዛት ለአቅራቢዎች ቅድሚያ የተከፈለ ቢሆንም አቅራቢዎቹ የተገለጹትን ማሽነሪና የላብራቶሪ እቃዎች በተለያዩ ምክንያቶች ሳያቀርቡ በመቅረታቸው የተከሰተ በመሆኑ ይንንም ችግር ለመቅረፍ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተነጋግረው መፍትሄ የሚሰጡት መሆኑን፣
- የተለያዩ በሂሳብ መደብ /4274/ የሚታየውን ሂሳብ በየወሩ ከሚመለከታቸው ሰራተኞች ሰብስበው ለሚመለከተው ክፍል ገቢ የሚያደርጉ መሆኑን፣

ለሥራ አመራር ደብዳቤ በላኩት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

4. <u>ተከፋይ ሂሳብ፣</u>

4.1 <u>ግኝት፣</u>

የዩኒቨርስቲው ተከፋይ ሂሳብ በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሒሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሠረት የተያዘ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱ ሁኔታዎች ተገኝተዋል።

- በሂሳብ መደብ 5002 /ልዩ ልዩ ተከፋይ ሂሳብ/ የተያዘ ብር **561,546.41** በተለያዩ ድርጅቶችና ግለሰቦች ስም ያለ ሲሆን ከሶስት ዓመት በላይ እየተንከባለለ የመጣና እስከአሁን ድረስ ያልተወራረዱ መሆኑ ታውቋል።

4.2 ሥጋት፣

- ሂሳብ በወቅቱ ካልተወራረደ ወይም ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ ካልተወሰደበት የሂሳብ ሪፖርቱን ተአማኒነት ሊያሳጣው ይችላል፡፡
- ግዴታ የተገባባቸው ሂሳቦች በወቅቱ ሂሳባቸው መወራረድ ካልቻለ ተጨማሪ ወጪን እና ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡
- ተከፋይ ሂሳብ ሳይወራረድ ከአንዱ በጀት ዓመት ወደ ሌላ በጀት ዓመት መተላለፉ የሂሳብ ክምችት ከመፍጠሩም በላይ የተከፋዩ ዝርዝር ሁኔታ እንዳይታወቅ ሊያዳርግ ይችላል፡፡ የተቀመጠውንም ገንዘብ ለብክነት ሊዳርግ ይችላል፡፡

4.3 የማሻያ ሀሳብ፣

- በፋይናንስ አስተዳደር ደንብና መመሪያ መሠረት ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ ለሚመለከተው አካል መከፈል ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ የማይሆን ከሆነ ግን የተከፋይ ሂሳቡ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

4.4 የሥራ አመራሩ ምለሽ፤

የሥራ አመራሩ በተከፋይነት የሚታየው የገንዘብ መጠን አጣርተው ለባለመብቱ ወይም ለተፈቀደለት አገልግሎት ሥራ ላይ እንዲውል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ውሳኔ እንዲሰጥበት የሚያደርጉ መሆኑን ለሥራ አመራር ደብዳቤ በላኩት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

5. የበጀት ሂሳብ፣

5.1 ግኝት፣

የዩኒቨርሲቲው የበጀት አስተዳደር እና አጠቃቀም በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 እና በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 ክፍል 3 አንቀጽ 12 መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከተው ተገኝቷል፡፡ በበጀት ዓመቱ ለዩኒቨርሲቲው ተስተካክሎ የተፈቀደው እና ሥራ ላይ የዋለው በጀት ሲነጻጸር፤

- ከመደበኛ በጀት ብር 19,982,427.02፣ ከካፒታል በጀት ብር 124,431,172.13 እና ከውስጥ ገቢ ብር 51,843.61፣ በድምሩ ብር 144,465,442.76 በየሂሳብ መደቡ ከ10% በላይ ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፤

- ከመደበኛ በጀት ብር 8,610,801.77 እና ከውስጥ ገቢ ሂሳብ ብር 1,059,558.59፣ በድምሩ ብር 9,670,360.36 ከተፈቀደው በጀት በላይ ሥራ ላይ የዋለ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ (ዝርዝር ሁኔታውም በአባሪ ቁ 1 ቀርቧል፡፡)

  በተጨማሪም **ከውስጥ ገቢ ሂሳብ** ከበጀት በላይ ከወጣው ብር 1,059,558.59 ውስጥ በሂሳብ መደብ 6211 የወጣው ብር 8,648.00 እና በሂሳብ መደብ 6216 የወጣው ብር 231,731.40፣ በድምሩ ብር 240,379.40 አስቀድሞ በጀት ሲደለደል በጀት ባልተያዘባቸው የሂሳብ መደቦች ላይ የወጣ መሆኑ ታውቋል፡፡

5.2 ስጋት፣

- የበጀት ዝውውር ሣይደረግ ወይም ተጨማሪ በጀት ሳይፈቀድ ከተፈቀደው በጀት በላይ መጠቀም እዲሁም በጀት ባልተያዘበት የሂሳብ መደብ ወጪ ማውጣት መመሪያን ከመጣሱም ባሻገር የመንግሥትን ውስን ሀብት ለብክነት ሊያጋልጥ ይችላል፡፡
- የወጪ በጀቱ በእቅዱ መሠረት ሥራ ላይ እንዲውል አለመደረጉ የዩኒቨርሲቲውን ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ የበጀት ዕቅዱ ትክክለኛነት ላያመለክት ይችላል፡፡

5.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- ለወደፊቱ አሰራሩ እንዲስተካከል እና የዩኒቨርሲቲው ዕቅድና ክንውን የተጣጣመ እንዲሆን ሊደረግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም በበጀት ዕቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲሁም ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

5.4 የሥራ አመራሩ ምለሽ፤

የሥራ አመራሩ፣

- *ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት ያጋጠማቸው አቅራቢዎች በወቅቱ የሚፈለገውን አቅርቦት ባለማቅረባቸው እና ክፍያ ባለመፈጸሙ ሲሆን በአንዳንዶቹ ላይ በታቀደው መሰረት ባለመተግበሩ የተከሰተ መሆኑን፣*
- *ከበጀት በላይ የተከሰተው በአንዳንድ የወጪ መደቦች ላይ ፍላጎቱ እና የተስተካከለው በጀት ባለመጣጣሙ የተከሰተና በወቅቱ በጀት ዝውውር ለማድረግ ባለመቻላቸው የተከሰተ መሆኑን፣*

- የካፒታል በጀት አፈጻጸምን በተመለከተ የኮንትራክተሮች የመፈጸም አቅም ዝቅተኛ በመሆኑ እና አዲስ ወደ ሥራ የሚገቡ ግንባታዎች በዲዛይንና በሌሎች ምክንያቶች በመዘግየታቸው በጀቱን ሥራ ላይ ሳያውሉ መቅረታቸውን፣
- ባጠቃላይ ከበጀት በላይ የተጠቀሙት በወጪ አርዕስት እንጂ በፕሮግራም ሲታይ ከበጀት በላይ ያልወጣ በመሆኑ በዚህ ዕይታ እንዲታይላቸው እና ቀጣይ የበጀት አፈጻጸማቸውን የሚያስተካክሉ መሆኑን፣

6. <u>የንብረት አስተዳደር</u>፣

6.1 <u>አላቂና ቋሚ ዕቃዎች እንዲሁም የተማሪዎች ክሊኒክ</u>፣

6.1.1 <u>ግኝት</u>፣

የዩኒቨርሲቲው የንብረት አስተዳደር በመንግስት የንብረት አመዘጋገብ፣ አያያዝ እና አጠባበቅ አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 በተገለፁት ሁኔታዎች እና ድንጋጌዎች መሠረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግት፣

<u>ቋሚ ንብረት</u>

- በቋሚ ዕቃ ግምጃ ቤት የንብረት ገቢ ሞዴል 19 እና ወጪ ሞዴል 22 የሚሰራው በአንድ ሰራተኛ ብቻ መሆኑ፤
- የእስቶክ ካርድና የቢን ካርድን ጨምሮ ምንም ዓይነት ንብረት ምዝገባ የማይከናወን በመሆኑ ያለውን ባላንስ /ሚዛን/ ለማወቅ የማይቻል መሆኑ፤
- የበጀት ዓመቱ ዓመታዊ ንብረት ቆጠራ ያልተካሄደ መሆኑ፤
- አዲስ አገልግሎት ላይ ያልዋሉ በቁጥር ወደ 20 የሚሆኑ UPS ያለ አገልግሎት በእስቶር ውስጥ ያሉ መሆኑ፤
- በቁጥር 200 የሚሆኑ ያገለገሉ ግን የአገልግሎት ጊዜያቸው ያላበቃ የካፍቴሪያ ወንበሮች ያለስራ አስቶር ወስጥ መሆናቸው፤
- ብረት ድስት፤ የሻይ ማንቆርቆሪያ፤ የመመገቢያ ሰሀን የመሳሰሉት በርካታ ቁጥር ያላቸው የምግብ ቤት ዕቃዎች አገልግሎት ያቆሙ ቢሆንም ሳይወገዱ ሜዳ ላይ የተቀመጡ መሆኑ፤
- እንደ ቁም ሳጥኖች፤ ጠረጴዛዎች፤ ወንበሮችና ሌሎች የተለያዩ ቁሳቁሶች መወገድ እያለባቸው ሳይወገዱ ተበታትነው ሜዳ ላይ የሚገኙ መሆኑን፤

አላቂ ንብረትን በተመለከተ

- ብዛታቸው 700 የሚሆን ለሰራተኞች የደንብ ልብስ ተብሎ የተገዙ የወንድና የሴት ጥንድ ጨማዎች ለሰራተኛው ሳይከፋፈል ከ2 ዓመት በላይ ያለአገልግሎት እስቶር ወስጥ የተከማቹ መሆኑ፣

የተማሪዎች ክሊኒክ መድኃኒት ክፍልን በተመለከተ

- የመድኃኒት አጠቃቀምን በተመለከተ የገቢና የወጪ አጠቃቀም በወሩ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት የማይደረግ መሆኑ፤በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

6.1.2 ስጋት፣

- የዩኒቨርሲቲው የንብረት አያያዝ፣ አመዘጋገብ እና አጠባበቅ በመመሪያው መሠረት ተፈፃሚ ካልሆነ ሁኔታው ንብረቶቹን ለከፋ ብልሽትና ብክነት ይዳርጋል፤ ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍትም ይችላል፡፡
- የመድኃኒት የገቢና የወጪ አጠቃቀምን በተመለከተ በየጊዜው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት የማይደረግ ከሆነ መድኃኒቶቹ ለብክነት ከተዳረጉ ወቅታዊ እርምጃ ላይወሰድባቸው ይችላል፡፡

6.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- የቢን ካርድና እስቶክ ካርድ የቁጥጥር የአሰራር ስርዓት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ለበርካታ ጊዜ ያለ አገለልግሎት በየቦታው ወድቀው የሚገኙ ንብረቶች ትኩረት ተሰቷቸው ሊወገዱ ይገባል፡፡
- ንበረቶች ለብክነት እንዳይደረጉ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡
- ጥቅም ላይ መዋል እየቻሉ ያልዋሉ ንብረቶች ጥቅም ላይ ሊውሉ ይገባል ፡፡
- የመድኃኒት የገቢና የወጪ አጠቃቀም ወቅታዊ ሪፖርት በተወሰነ ወቅት ለሚመለከተው አካል መድረስ ይኖርበታል፡፡

6.1.4 የሥራ አመራሩ ምለሽ፤

የሥራ አመራሩ፣

- ባለው የሰው ኃይል እጥረት ምክንያት ቀደም ሲል የቋሚም ሆነ የአላቂ ግምጃ ቤት ሥራ በአንድ ሰው ሲከናወን የነበረ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በBPR በተደረገው የሰው ኃይል አደረጃጀት ሰራተኞች እየተመደቡ የሚገኙ በመሆኑ በቀጣይ የዚህ አይነቱ ክፍተት የሚስተካከል መሆኑን፣

- ከላይ በተጠቀሰው የሰው ኃይል እጥረት ምክንያት የስቶክ መዛግብቶች በአግባቡ ባለመሰራታቸው ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት አለመቻሉን፣ ይህም ሁኔታ ዩንቨርሲቲው ከተቋቋመውበት ጊዜ ጀምሮ የነበረው ንብረት በሙሉ ባጠቃላይ ቆጠራ ለማካሄድ ሲባል በወቅቱ ቆጠራው ያልተከናወነ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ያለውን የሰው ኃይል አደረጃጀት በመጠቀም ቆጠራውን ለማከናወን በዝግጅት ላይ እንደሚገኙ፣
- ማንኛውም ዕቃ ለተገዛበት ዓላማ አገልግሎት ላይ ማዋል እንዳለበት የሚታወቅ በመሆኑ ተጠቃሚው ክፍል በግዥ ፍላጎት እቅድ መሰረት የተገዙትን አቅርቦቶች በወቅቱ አውጥቶ አገልግሎት ላይ እንዲያውሉ እንደሚደረግ፣
- የካፍቴሪያ ወንበሮችን በተመለከተ አካል ጉዳተኞች ያስተዳድሩት በነበረው ካፍቴሪያ በአሁኑ ወቅት ለቀው የሄዱ በመሆኑ ግምጃ ቤት ተመላሽ የተደረገ ንብረት መሆኑን፣
- የሚወገዱ ንብረቶችን በተመለከተ ዩኒቨርሲቲው በተሰጠው ስልጣን መሰረት የማስወድ ስራ ሂደት የተጀመረ ቢሆንም በተያዘለት ጊዜ ገደብ ባለመጠናቀቁ ለመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ያሳወቁ ቢሆንም ጊዜውን የማራዘም ስልጣን እንደሌለው ያሳወቁ በመሆኑ ሂደቱ ባለበት ሊቆም እንደሚችል፣ ሆኖም ግን ከዚህ ውጭ ያለው ሥራ ለመሥራት እተሞከረ መሆኑን፣
- ያገለገሉ ዕቃዎች ተመላሽ ሲደረጉ የሚቀመጥበት መጋዝን ለመስራት ዩኒቨርሲቲው በዝግጅት ላይ እንደሚገኝ፣
- የተማሪዎች ምግብ ቤትን በተመለከተ የአቅርቦቱ መጠን የሚረጋገጥበት ሚዛን ዕጥረት ቢኖርም አንድም ዕቃ ሳይመዘን ገቢ የማይደረግ መሆኑና የሚዛን ግዥም በሂደት ላይ መሆኑን፣
- የሰራተኞች የደንብ ልብስ ጫማ ግዥ ሲፈፀም በአመቱ ውስጥ ያሉትን ሰራተኞች ቁጥር እና አዲስ የሚቀጠሩ ሰራተኞችን ታሳቢ አድርጎ የሚፈፀም በመሆኑ ያሉት ሰራተኞች የደንብ ልብስና ጫማ ተጠቃሚ የሆኑ ሲሆን እቅዱ ተግባራዊ ከሆነ በኋላ ግን ከስራ የሚለቁ እና አዲስ ይቀጠራሉ ተብሎ የተገመተው ሳይገኝ ሲቀር በታሳቢ የተገዛው በትርፍነት የተቀመጠ በመሆኑ በአሁኑ ወቅት ለሰራተኛው ለመስጠት በማነጅመንት ውሳኔ እንዲሰጥበት መቅረቡን፣

- ከስቶር ወደ Dispensary በInternal facility Report Form የሚወጣ ሲሆን ይሄውም መዲሀኒቱ ተመዝግቦ እንደሚወጣ፣ ከ Dispensary ለተማሪዎች በሚሰጥበት ወቅት በመዲሃኒት ማዘዣው ላይ ተማሪው ስሙን ጽፎ የሚፈርም ሲሆን የየዕለቱ አጠቃቀማቸው በመመዝገቢያ /Regstration form/ ላይ የሚመዘገብና የየዕለቱ የመዲሃኒት ማዘዣው ተቋጥሮ እንደሚቀመጥ፣ ነገር ግን ከዚህ ወር በኃላ አዲስ ፎርም አዘጋጅተው የመድሃኒት አጠቃቀማቸው እስከሚመለከተው ክፍል የሚያሳውቅ እንደሚሆን፣

በላኩት ምላሽ ገልጸዋል።

6.2 የተሽከርካሪዎች አያያዝ፣

6.2.1 ግኝት፣

የዩኒቨርስቲው ተሽከርካሪዎች በፌደራል መንግስት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 መሠረት መያዛቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ኢት-4 16638 Mistubish pick up ተጋጭቶ ከአንድ ዓመት በፊት በኢትዮ ኒፖን (Ethionipon) ለጥገና እንደገባና እስከአሁን ተጠግኖ ያልወጣ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል።

6.2.2 ሥጋት፣

- ተሽከርካሪው በወቅቱ ክትትል ተደርጎበት ተጠግኖ ካልወጣ ዩኒቨርሲቲው በዋጋ ለውጥ ምክንያት ለተጨማሪ ወጪ ሊዳረግ ይችላል። ተሽከርካሪው ተጠግኖ ባይወጣ ሊሰጥ የሚችለው አገልግሎት ሊስተጓጓል ይችላል። ክትትል በሚያደርጉበት የሥራ ኃላፊዎች ለውጥ ምክንያት ተረስቶ ባለበት ሊቀርም ይችላል።

6.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ተሽከርካሪው ተጠግኖ እንዲወጣ ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል።

6.2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

- የሥራ አመራሩ ኢት 4-16638 Mistubish pick up በተመለከተ በ CEP ዳይክቶሬት ጥያቄ ሞጅል ለተማሪዎች በየክልል ለመበተን በመሄድ ላይ እያለች ወለጪቲ አከባቢ በጉዞ ላይ ጎማ በመፈንዳቱና በመገልበጧ ምክንያት በመድን ኢንሹራንስ ድርጅት በኩል Recovery ስራው ብዙ ጊዜ በመፍጀቱ ቶሎ ጥገና አገኝቶ ስራ ላይ ማዋል ባይቻልም አሁን የሪከበሪው ስራ ተጠናቆ መድን

ድርጅት ለጥገና በኢትዮ ኒፖን ያስገባትና ጥገናውንም የዩኒቨርሲቲው ጠ/አገልግሎት ት/ሰ/ተ/ጥ/ቡድን እየተከታተለ እንደሚገኝ በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

7. <u>እርምጃ ያልተወሰደባቸው የ2008 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች</u>፣

7.1 <u>ግኝት</u>፣

በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 ክፍል 2 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2(በ) መሠረት የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች በውጭ ኦዲት ወይም በውስጥ ኦዲት ሪፖርት በተመለከተው መሠረት አስፈላጊውን እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት እንዳለባቸው ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ውስጥ፣

- ለፍሳሽ ውሃ ማጣሪያ ፕላንት ግንባታ ስራ በ30/10/08 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 554654 ለአዲስ ገላው ለሕንጻ ስራ ተቋራጭ በምስክር ወረቀት /payment certificate/ 33 እና 34 የተከፈለ ብር 17,943,350.74 ውስጥ ለብር 16,732,085.40 የክፍያ ደረሰኝ ያልቀረበ መሆኑ፣
- ለግንባታ ሥራ ከውጪ ተገዝተው የገቡ የግንባታ ዕቃዎች ማጓጓዣ ለአንለይ አለሙ የደረቅ ጭነት ማመላለሻ ድርጅት ከተከፈለው ብር 2,201,216.24 የብር 1,705,431.54 የክፍያ ደረሰኝ ያልቀረበለት መሆኑ፣
- የዕቃ ግዥና የህንጻ ግንባታ የጉዳት ካሳን በተመለከተ መላክ የት/ቤት ላብራቶሪ ዕቃዎች ጅምላ አከፋፋይ ኃ/የተ/የግል ማህበር ከተቋሙ ጋር በገቡት ውለታ መሰረት ባለመፈጸማቸው ከአቅራቢዎቹ ያልተሰበሰበ የጉዳት ካሳ ብር **69,331.00** ያልተሰበሰበ መሆኑ፣
- ዩኒቨርሲቲው በውሉ መሰረት በተቀመጠው የማስረከቢያ ቀን መሰረት ግንባታውን አጠናቀው ያላስረከቡ 5 የህንጻ ተቀራጮች የህንጻ ግንባታውን ላዘገዩበት የጉዳት ካሳ/ቅጣት/ በድምሩ ብር 22,945,687.00 እንዲከፍሉ ያላደረገ መሆኑ፣
- የብር 1,261,600.25 በተለያዩ የሂሳብ መደቦች በጊዜ ገደብ ያልተወራረደ የተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ፣
- ብዛት ያላቸው የግንባታ ብረቶች በዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ላይ ተከማችተው ለብልሽት ተጋልጠው የሚገኙ መሆኑን መወገድ ያለባቸው በርካታ ተለያዩ

ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች፣ አሮጌ ቆርቆሮዎች፣ የተለያዩ ብረታ ብረቶች፣ የውሃ ፕላስቲኮች፣ የአጥር ሽቦዎች፣ የፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎች፣ አሮጌ ጎማዎች እና ፓኔሎች የሚገኙ መሆኑ፣

- የሠሌዳ ቁጥሩ ኢት 4-0109 የሆነ 1 ሞተር ሳይክል በብልሽት ምክንያት አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑ፣

በሚሉ ግኝቶች ላይ እስከ 2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ማብቂያ ጊዜ 25/03/2010 ድረስ እርምጃ ያልተወሰደባቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

7.2 ስጋት፣

በኦዲት ግኝቶች ላይ አፋጣኝ የእርምት እርምጃ አለመውሰድ፡-

- ከፍተኛ ገንዘብና ጊዜን ለኪሳራ ሊዳርግ የሚችል ነው፡፡
- ለመንግሥት ገንዘብ መጥፋትና መጉደል መንገድ የሚከፍት አሠራር በመሆኑ ተጠያቂነትንም ሊያስከትል ይችላል፡፡
- በሕግ፣ በደንብና መመሪያ ላይ በመመስረት የተሰጡ የኦዲት አስተያየቶችን ሥራ ላይ አለማዋል የተሻለ አሠራርን መከተል አያስችልም፡፡

7.3 የማሻሻያ ሃሳብ፤

የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ከፍተኛ ገንዘብና ጊዜ የወጣባቸው በመሆኑ በኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ላይ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድ የሥራ አመራሩ፣ የዩኒቨርስቲው ቦርድና የሚመለከታቸው የበላይ ኃላፊዎች ለጉዳዩ ትኩረት መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

7.4 የሥራ አመራሩ ምለሽ፤

የሥራ አመራሩ፣

- የቆሻሻ ውሃ ማጣሪያ ግንባታ ስራ ዩኒቨርሲቲውን ወክሎ ሲያሰራና ክፍያውንም ሲፈፅም የቆየው GIZ-IS ሲሆን ክፍያ የፈፀመበትንም ሰነድ ለዩኒቨርሲቲው የላከ ቢሆንም ክፍያውን ሲፈፅም በባንክ በኩል በመሆኑ ከሰነዱ ጋር የባንክ አድቫይሱ የተያያዘ ሲሆን ኮንትራክተሩ የቆረጠው የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ባለመያያዙ ሰነዱን እዲልኩልን ለ GIZ-IS ጥያቄ ያቀረቡ እና መልሱን እየጠበቁ መሆኑን፣
- የጉዳት ካሳን በተመለከተ ከተጠቀሱት ኮንስትራክሽን ድርጅቶች እና ከአቅራቢዎች ለመሰብሰብ አፈፃፀሙን ለመከታተል ጉዳዩ ለዩኒቨርሲቲው ህግ ክፍል የተመራ ሲሆን ውጤቱንም ተከታትለው ለሚመለከተው ክፍል የሚያሳውቁ መሆኑን፣

- በተለያዩ ተሰብሳቢ ሂሳቦች የተገለፀው የገንዘብ መጠን በ2009 በጀት ዓመት መጨረሻ ብር 378,945.65 መሆኑን ገልታ ረጅም ጊዜ ሳይወራረድ የቆዩትን ከተሰብሳቢ ሚዛን ላይ ለመቀነስ አስፈላጊውን አስተዳደራዊ እርምጃ ለመውሰድ እየተንቀሳቀሱ መሆኑን፣
- የግንባታ ብረታ ብረቶች የዩኒቨርሲቲው ንብረት ሳይሆኑ የተለያዩ ኮንትራክተሮች ግቢ ውስጥ ጥለውት የወጡት በመሆኑ የንብረቶቹ ባለቤቶች ተለይተው እንዲያነሱ እንደሚደረግ፣ ሌሎች ብረታ ብረቶች እንዲወገዱ ከንብረት ማስወገድ አገልግሎት ጋር ተነጋግረው በከፊል የተወገደ ሲሆን አሁንም የተቀረውን ለማስወገድ ጥረት እያደረጉ መሆኑን፣
- ሞተር ሳይክሏ ተጠግና አገልግሎት እንድትሰጥ እየሰሩ መሆኑን፣

በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

በመጨረሻም ለተደረገልን መልካም የስራ ትብብር እናመሰግናለን!

አባሪ ቁ 1

	ከመደበኛ በጀት ከበጀት በላይ የወጣ			
የሂሳብ መደብ	የተስተካከለ በጀት	ሥራ ላይ የዋለ	ከበጀት በላይ የወጣ	በመቶኛ
6114	1,759,500.00	1,803,491.20	43,991.20	3
6216	56,350,000.00	62,938,201.96	6,588,201.96	12
6231	14,015,000.00	15,560,187.23	1,545,187.23	11
6259	3,000,000.00	3,433,421.38	433,421.38	14
ድምር	**75,124,500.00**	**83,735,301.77**	**8,610,801.77**	
ከመደበኛ በጀት ያልተሰራበት በጀት				
የሂሳብ መደብ	የተስተካከለ በጀት	ሥራ ላይ የዋለ	ያልተሰራበት	በመቶኛ
6113	1,000,000.00	108,326.00	891,674.00	89
6121	36,663,002.00	30,497,303.08	6,165,698.92	17
6123	100,000.00	18,944.20	81,055.80	81
6131	15,738,863.60	13,970,068.86	1,768,794.74	11
6211	5,000,000.00	2,590,885.36	2,409,114.64	48
6213	2,050,000.00	1,740,976.01	309,023.99	15
6214	2,012,500.00	975,078.82	1,037,421.18	52
6218	2,515,000.00	1,932,480.67	582,519.33	23
6219	1,185,000.00	1,058,785.82	126,214.18	11
6223	1,305,000.00	620,774.61	684,225.39	52
6232	4,730,000.00	3,452,336.82	1,277,663.18	27
6241	2,840,000.00	2,479,537.31	360,462.69	13
6243	450,000.00	154,052.20	295,947.80	66
6251	4,300,000.00	3,706,275.35	593,724.65	14
6253	700,000.00	402,768.77	297,231.23	42

6255	230,000.00	198,593.60	31,406.40	14
6256	850,000.00	732,437.29	117,562.71	14
6257	2,000,000.00	912,436.24	1,087,563.76	54
6271	3,005,000.00	1,349,116.24	1,655,883.76	55
6412	475,000.00	384,031.55	90,968.45	19
6417	325,000.00	206,729.78	118,270.22	36
ድምር	**98,894,665.60**	**44,558,564.70**	**19,982,427.02**	
ከካፒታል በጀት ያልተሠራበት በጀት				
6313	84,250,000.00	66,032,840.06	18,217,159.94	22
6314	20,675,000.00	3,293,110.79	17,381,889.21	84
6321	10,500,000.00	412,897.44	10,087,102.56	96
6323	146,980,000.00	68,234,979.58	78,745,020.42	54
ድምር	**262,405,000.00**	**137,973,827.87**	**124,431,172..13**	
ከውስጥ ገቢ ከበጀት በላይ የወጣ				
የሂሳብ መደብ	**የተስተካከለ በጀት**	**ሥራ ላይ የዋለ**	**ከበጀት በላይ የወጣ**	**በመቶኛ**
6116	9,000,000.00	9,693,825.38	693,825.38	8
6211		8,648.00	8,648.00	100
6216		231,731.40	231,731.40	100
6231	220,000.00	255,097.85	35,097.85	16
6233	20,000.00	36,407.36	16,407.36	82
6353	95,000.00	160,973.60	65,973.60	69
6258		4,275.00	4,275.00	100
6271		3,600.00	3,600.00	100
ድምር	**9,335,000.00**	**10,394,558.59**	**1,059,558.59**	

ከውስጥ ገቢ ያልተሠራበት በጀት				
የሂሳብ መደብ	የተስተካከለ በጀት	ሥራ ላይ የዋለ	ሥራ ላይ ያልዋለ	በመቶኛ
6121	50,000.00	39,184.33	10,815.67	22
6256	10,000.00	8,972.06	1,027.94	10.28
6412	70,000.00	30,000.00	40,000.00	57
ድምር	**440,000.00**	**357,503.24**	**51,843.61**	